
ኢትዮ - ትረካ
ከንኪን ዳና ሞዐጡ ! !
@ethio_terka
TAFT
PHOTOGRAPHY

እንደ በግ እየተነዳች ሄደች። የት እንደምትሄድ ታውቃለችን? አታውቅም። ነገር ግን የምታውቀው ነገር ቢኖር የእነዚያን ጨካኝ ሰዎች ሆቴል ቤት ለቅቃ መውጣትዋን ነው። ከቤት ስትወጣ «ደህና ሁኝ» ያሳት ሰው አልነበረም። እርስዋም «ደህና ሁኑ» ብላ የተሰናበተችው ሰው የለም። ከዚያ ቤት ተጠልታና ጠልታ ነው የወጣችው።

ከዚት ሰማይ ሰማዩን እያየች ሰውዬውን ተከትላ ሄደች፤ ነጐደች። አልፎ አልፎ ደጉን ሰውዬ ቀና ብላ ታየዋለች። የእግዜር መልእክተኛ መሰላት።

መሸት ሲል ዣን ቫልዣ ልጅትዋን ይዞ ከፓሪስ ከተማ ደረሰ። ከተማ አንደገቡ በጋሪ ተሳፍረው ከከተማው ክልል ወጡ። እርሱ ከፈለገበት ቦታ ሲደርሱ ለባለጋሪው ሂሣባቸውን ከፍለው ወረዱ። ዣን ቫልዣ የልጅትዋን እጅ ይዞ ጥቂት ከተጓዙ በኋላ ከአንድ አልቤርጎ ገቡ። አራታቸውን በለ። ብዙ ስለተጓዙ ደክሞአቸዋል። ከዚት እንደደኩማት ስለተገነዘበ አቀፋት፤ አሷም አሻንጉሊትዋን ታቀፈች። ወዲያው ከጐርን ቫልዣ እጅ ላይ እንቅልፍ ይዞአት ሄደ።

❀❀❀

ምዕራፍ አሥር

አሮጌው ቤት

ከአርባ ዓመት በፊት እጅግ ጭር ያለ ስፈር የነበረው ዛሬ ብዙ ሕዝብ ይተራመስበታል። ንጠር መሆኑ ቀርቶ ወደ ከተማነት ተለውጧል። አካባቢው ዣን ቫልዣ ሲያውቀው ከፓሪስ ከተማ ጠጣ ያለ ባላገር ነበር። ዛሬ የከተማው አካል ሆኖአል። ብዙ ቤቶች ተሠርተዋል፤ መንገድም ወጥቶለታል። ቢሆንም ግን የገጠርነት ስሜት አሁንም ይታያቢታል። ከመንገዱ ግራና ቀኝ ሳር በቅሉአል። ቤቶቹም ቢሆኑ እስከዚህም የጸዱ አይደሉም። የፈረስ ገበያ ከዚያ አካባቢ ስለነበር የሥፍራው ጽዳት ይህን ያህል አያስደስትም።

ከዋናው መንገድ ትንሽ ራቅ ብሎ የሚታይ ባለአንድ ፎቅ አሮጌ ቤት አለ። በሮቹ በምስጥ ስለተበሉ አልፎ አልፎ ቀዳዳ ይታይባቸዋል። የቤቱ መስኮቶች በጣም ሰፋፊ ናቸው። የመስኮቶቹ መስታወት እንዳንድቹ ስለተሰበሩ በካርቶን መሳይ ወረቀቶች ተሸፍነዋል። መጋረጃዎቹም ቢሆን ከመበለዛቸውም በላይ ሚዳ ጣፋቸው ተቀዳዶዋል። ወደ ፎቅ በሚያስወጣው

መሰላል ሲራመዱ ደረጃው እንደ ሙዚቃ መሣሪያ ይጮኣል። በረት የመሰለ ትልት ከፍል ከሩቁ ይታያል። የዚህ ክፍል ሁለቱም መስኮቶች ሰፋፊ ሲሆኑ ዚያ በኩል ወደ ውጭ በማየት በመንገድ የሚያልፈውን ማየት ይቻላል። ቤቱ ቁጥር 50-52 ነው።

ዣን ቫልዣ ከዚህ አሮጌ ቤት አጠንብ ሲደርስ ቆም ብሎ ቤቱን አየው። ጭልፊት የሚያሳድዳት ጫጪት የተሰወረ ከሰላ እንደምትፈልግ ሉቱ እርሱም ከዣቫቬር ለመሰወር ከሰላ ይፈልጋል። የዚህ ቤት አቀማመጥ ደግሞ በጣም የተሰወረ ስለነበር የሚፈልገውን ያገኘ መሰለው። ከኪሱ ቁልፍ አውጥቶ በሩን ከፈተው። ከገባ በኋላ መልሶ ዘጋው። ከዚትን ታቴ በደረጃው ወደ ፎቅ ወጣ። ደረጃውን ወጥቶ ሲጨርስ ሌላ ቁልፍ ከኪሱ አወጣ። የተቆለፈውን በር ከፍቶ ወደ አንድ ክፍል ገባ።

ስፋ ካለ ክፍል ወለል ላይ ትልቅ ፍራሽ ተዘርግቷል። ጥቂት ብርድና ጠረጴዛም አለ። የአላት ማንደጃ ከአንድ ጥግ ይታያል። አንድ ተጀ የልጅ አልጋም አለ። ዣን ቫልዣ ቀስ ብሎ ከዚት ሳትነቃ ከትጀሽ ሌጋ ላይ አስተኛት።

በሩን መልሶ ከዚጋ በኋላ ሻማ አበራ። የመንገዱ መብራት ክፍሉን ያይ ስለነበር ሻማ እስከበራ ድረስ በጨለማ አልተንገዳገደም። በአለፈው ጊ እንዳደረገው ሁሉ ከዚት ተኝታ ሳለ ዐይኑን ከዐይንዋ አላነሳም። ሄደም ጊዜ አፍጥጦ ተመለከታት። ከዚት ከማን ጋርና ዮት እንደተኛች ጥቀት ለብዙ ሰዓት እንቅልፍዋን ሰጠበች።

ዣን ቫልዣ ጎንበስ ብሎ እጅዋን ሳማት። ከዘጠኝ ወር በፊት ዘመላይ ሁኔታ እንቅልፍ ወስዶአት ሳለ የእናትዋን እጅ ስሞ ነበር። መሰላይ የሆነ የሀዘኔታና የፍቅንት ስሜት ተሰማው። ከዚት ከተኛችበት ሳጋ አጠንብ ተንበረከከ።

ወገግ ብሎ ነግቷል። ግን ልጅትዋ አሁንም እንቅልፍ እንደወሰዳት ነው። ከዐድ እቃ የጫነ ጋሪ በዚያ ሲያልፍ ያንን አሮጌ ፎቅ ቤት አነቃንቀው። ኒታው ቢጋይል ስለነበር እንኳን የተኛን የሞተን ይቀሰቅሳል ማለቱ ቷሮውን ብርታት መግለጽ እንጂ ማጋነን አይሆንም።

«እመት እመቤቴ» አለች ከዚት ፈንጠር ብላ ከአልጋው እየተነሳች። ሳብኛና ደግሞ «መጣሁ፤ መጣሁ» ስትል ፎንሽች። ዓይንዋን ሳትገልጥ ሳልጋው ዘልላ ወረደች። እየተንጠራራች ወደ ግድግዳው ሄደች።

«ወይ ጣጣ፤ መሞረጊያው የት አለ» አለች።

አሁን ዓይንዋን ገልጣለች። በፈገግታ ያጌጠ የዣን ቫልዣን ፊት

ተመለከተች።

«እህ! ለካስ...» አለች ልጅትዋ፤ «እንደምን አደሩ ጌታዬ።»

ቶሎ ብሎ አካባቢውን መላመድና ባለው መደሰት የልጆች ባህርይ ነው። ተደላች ሁነው ሰው ያስደስታሉ።

ከዜት ካተራንን ከአልጋዋ ስር አየቻት። ወዲያው ብድግ አድርጋ አቀፈቻት። ከአሻንጉሊቱ ጋር እየተጫወተች ዣን ቫልዣን የመዓት ጥያቄ ጠየቀችው። የት ነበረች? ፓሪስ ትልቅ ከተማ ነው? አሁን መዳም ቴናድዬ ከዚህ አይመጡም? ከዚህ የሚሰስ ቴናድዬ ቤት ምን ያህል ይርቃል? ሌላም፤ ሌላም። በመስኩቱ ወደ ውጭ አይታ «እንዴት ያምራል፤ እንዴት ደስ ይላል» ስትል ተናገረች።

የነበረችበት ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን ያስፈራ ነበር። ነገር ግን እርስዋ ነፃ የወጣች መሰላት።

«ቤቱን ልጥረግ?» ስትል ጠየቀች።

«የለም፤ ተጫወቺ» ሲል ዣን ቫልዣ መለሰላት።

ስትጫወት ቀኑ አለፈ። ስላለችበት ሥፍራም ሆነ ሁኔታ ለማወቅ ራስዋን ሳታስጨንቅ ከአሻንጉሊትዋ ጋርና ከጓደኛዋ ጋር እየተጫወተች ደስ ብሎአት ነበር የዋለችው።

በሚቀጥለው ቀን ጎሕ ሲቀድ እንዳለፈው ቀን ከዜት ስትነቃ ለማየት ዣን ቫልዣ ከአልጋው አጠገብ ሲቀመጥ አዲስ ስሜት ተሰማው። ዣን ቫልዣ ከዚያ በፊት ምንም ነገር አፍቅሮ አያውቅም። ትዳር ሳይዝ፤ ልጅ ሳይወልድ፤ ሴት ሳያፈቅርና የልብ ጓደኛ ሳያበጅ ለሃያ አምስት ዓመት ብቻውን ነው የኖረው። እስር ቤት ሆኖ ኑሮው የጨለማና የስቃይ ነበር። ዣን ቫልዣ እስር ቤት ከመግባቱ አስቀድሞ ከቤቱ ሲወጣ ልቡ በተስፋ የደነደነ፤ ሐሞተ-ሙሉ ሰው ነበር። አሁንና ልጆችዋ ከሕሊናው ጨርሰው ባይፋቱም በአሳብ የሚታዩት እጅግ ተንነው ሲሆን እነርሱን ለማግኘት ብዙ ጥረት አደረገ። ግን አላገኛቸውም። ጊዜ እንደሚሽረው እንደማንኛውም ነገር ከጊዜ በኋላ ግን ረሳቸው። ሌሎችም በወጣትነት ዘመኑ የሚያውቃቸው ነገሮች ሁሉ እንደዚሁ ከሕሊናው ውስጥ መንምነው ጠፍተዋል።

ከዜትን አግኝቶ ከዚያ የስቃይና የመከራ ኑሮ ሲያወጣትና ይዘኳት ሲሄድ ስሜቱ እጅግ ይነካል። ይህም ለሰው ልጅ የነበረውን ፍቅር ቀሰቀሰበት። የፍቅሩ ጽናት ከዚህች ልጅ ዙሪያ ተሰባሰበ። ወደ ከዜት አልጋ ጠጋ ብሎ አተኩሮ ሲመለከታት ልቡ በደስታ ፈካ። አናት ለልጅዋ ፍቅር እንደምትብረከረክ ሁሉ እሱም በዚህች ልጅ ፍቅር መዋጡ ገረመው።

የፍቅሩ ግለትና የሀዘኔታው ብዛት ሊገባውና በቃላት ሊገልጸው ከሚችለው በላይ ሆነበት።

እርሱ ሃምሳ አምስት ዓመቱ ሲሆን እርስዋ ስምንት ዓመትዋ ነው። ስለዚህ ፍቅሩ ግሪኮች አጋፔ ብለው የሚጠሩት አናት ለልጅዋ ያላት ፍቅር ዓይነት እንጂ የሌላ አልነበረም።

በሕይወት ዘመኑ ለሁለተኛ ጊዜ የሕይወት ተመስጦአዊና አስጨናቂ ትርኢት አየ። ከአስር ቤት ሲወጣ ያገኛቸው ጳጳስ የቀደዱለት የመጀመሪያው ፍጡር ናቸው። ከዜት ደግሞ ተጨማሪ የፍቅር ጎሕ ከፈተችለት። ይህንኑ እያሰላሰለ ጥቂት ቀናት አለፉ።

አሳዛኝዋና ምስኪንዋ ከዜትም ቢሆን ሳይታወቃት እየተለወጠች ነበረ። እናትዋ ጥላት ስትሄድ ጨቅላ ልጅ ነበረች። በዚያን ጊዜ ምን ትመስል እንደነበር ለማስታወስ አትችልም። ልጆች እንደ ሐረግ ካገኙት ላይ እንደሚጠመጠሙ ሁሉ አርስዋም ከሰዎች ላይ ተጠምጥማ ለማፍቀር ብትሞክርም ሰዎች የማፍቀር እድል አልሰጥዋትም ነበር። እነሚስተር ቴናድዬ፤ ልጆቻቸውና ሌሎችም ቢሆኑ ፍቅር አላሳይዋትም። ከዜታቸው የነበረውን ውሻ ትወደው ነበር። ግን አሱም ሞተ። ውሻው ከሞተ ጀምሮ እንኳን ሰው የቤት እንሰሳም ቢሆን አላቀረባትም። ስለዚህ ጥፋቱ የእርስዋ ባይሆንም ገና በስምንት ዓመትዋ ለሰው ፍቅር አልነበራትም። ቢወድዋት ኖን ትወድ ነበር፤ ምክንያቱም የማፍቀር ኃይል ስለነበራት ነው። ያንን ደግ ሽማግሌ ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ነው ያፈቀረችው። ፍቅሯ በየእለቱ እየጸበረ ሄደ። ከዚያ በፊት የማታውቀው ስሜት ተጠናወታት። ለእርስዋ ደጉ ጓደኛዋ አንድ ምስኪን ሽማግሌ ሳይሆን እጅግ የተዋበና ዕፁብ፤ ድንቅ የሆነ ዣን ቫልዣ የተባለ ሰው ነው።

በዣን ቫልዣና በዘዜት መካከል ያለው የእድሜ ልዩነት በሞላ ጉደል የሃሳ ዓመት ቢሆንም በሕይወት ዘመናቸው የደረሰባቸው ስቃይና መከራ፤ ምንም እንኳን ርዝማኔው ቢለያይም፤ አሳዛኝነቱ ተመሳሳይ ነው። ይህም አንድ እንዲሆኑና እንዲተራረቡ ምክንያት ሆናቸው። የከዜት ውስጣዊ ስሜት የሚመክበት አባት ሲፈልግ የዣን ቫልዣ ፍላጎትና ምኞት ደግሞ የደረሰበትን የሚያቃልልለት ልጅ ማግኘት ነበር። ስለዚህ የሁለቱ መገናኘት ማለት የፍላጎትና የስሜት መርካት ማለት ስለነበር ነፍሶቻቸው እርስ በእርስ የሚፈላለጉ መሆናቸውን አወቁ። ስሜታቸውን ለማርካት ተቃቀፉ።

በቃላት ኃይል ሁኔታውን አጥርቶ መግለጽ አይቻልም እንጂ ዣን ቫልዣ ማለት ሞት ተብሎ የተለቀሰለት አባትዋ ሲሆን ከዜት ማለት ደግሞ

የሙት ልጅ ናት። ስለዚህ ነው ዣን ቫልዣ የክዜት እውነተኛ አባት ባይሆንም የመንፈስ አባትዋ ሊሆን የቻለው። እንደ እውነቱ ከሆነ ክዜት በጨለማ ውሃ ለመቅዳት በሄደችበትና በሞትና በሽረት መካከል በነበረችበት ሰዓት ሊረዳትና ባልዲውን ከእጅዋ ወስዶ ሊሸከምላት ከየት መጣ ሳይባል በድንገት ብቅ ያለው ፍጡር መለኮታዊ ኃይል የሰጣት አባትዋ ነው።

ዣን ቫልዣ ለመደበቂያ ብሎ የመረጠው ቤት ተስማሚ ነበር። ከዚያ ሥፍራ ማንም ያገኘዋል ብሎ የሚጠራጠሩት ወይም ያጋልጠኛል ብለው የሚፈሩት አልነበረም። ዣን ቫልዣ ቤቱን እንዳለ አልተከራየውም። ምድር ቤቱን ነጋዴዎች እቃ ሞነው የመጡባቸውን ከብቶች ያሳድሩበታል። ፎቁ ላይ ብዙ ክፍሎች ያሉት አፓርትመንት ቢሆንም ከእነርሱና ከእንዲት አሮጊት በስተቀር ሌላ ሰው አልነበረበትም። አሮጊትዋም ብትሆን የዣን ቫልዣ ሠራተኛ ነበረች። የተቀሩት ክፍሎች ባዶ ናቸው።

አሮጊትዋ የቤቱም ጠባቂ ሁና ትሠራ ስለነበር የነበሩበትን ክፍል ያከራየቻቸው ይህቺ ቤት ናት። እንደ አጋጣሚ ቤቱን የተከራዩት የግና እለት ነበር። ዣን ቫልዣ ራሱን ሲያስተዋውቅ ከሩቅ አገር የመጣ፣ ክስረት የደረሰበት ነጋዴና የሚኖረውም ከልጅ ልጁ ጋር እንደሆነ አድርጎ ነው። የስድስት ወር የቤት ኪራይ በትድሚያ ከፈለ። ቱኑ አልፎ ሳምንት፣ ሳምንት አልፎ ወራት ተተኩ። ክዜትና ዣን ቫልዣ ከዚያ አስቀያሚ ቤት ደስ አያላቸው ኖሩ።

በጠዋት ተነስቶ እንደሚያዜም ወፍ ክዜትም በጠዋት እየተነሳች ትጫወታለች፣ ትስቃለች፣ ትዘፍናለች። አንዳንዴ ዣን ቫልዣ እጅዋን እየያዘ ያንሸራሽራታል። ሕይወትዋን ሙሉ በግሣሄና በድብደባ ያሳለፈች ልጅ አሁን ኑሮ በድንገት ስለተለወጠላት አንዳንዴ ግር አያላት እንደማፈር ትላለች።

ክዜት እንደ ድሮው የተቦጫጨቀ ቡትቶ አትለብስም። እንደ ሀዘነተኛ ጥቁር ነው የምትለብሰው። ጥቁር ይሁን እንጂ ማራኪ ልብስ ስለሆነ አምሮባታል። ከድህነት ወጥታ የኑሮን ምንነት እየቀመሰች ነው።

ዣን ቫልዣ ፊደል ያስቆጥራት ጀመር። ራሱ ፊደል የቆጠረው እስር ቤት ሆኖ ነው። ክዜትን ማስተማርና መጠበቅ የዣን ቫልዣ የእለት ተእለት ተግባር ሆነ። አንዳንዴ ቁጭ ብለው ሲጫወቱ ስለእናትዋ ያወጋታል። በጸሎትዋ እንድታስባት ያስተምራታል። እሷም «አባባ» እያለች ነው የምትጠራው። ይህ እንግዲህ የራስዋ ግምት እንጂ የነገራት አልነበረም።

ዣን ቫልዣ ክዜትን አግኝቱ ባፈቀራትና በራራላት ጊዜ የነበረበትን ሁኔታ መግለጽ ተገቢ ይሆናል። ክዜትን ያገኘት የሰውን ልጅ ክፉነት፣

ጭካኔተስብን ጭካኔና ችግር፣ እንዲሁም የኑሰምን አንዱን ገጽታ ብቻ ብቻ ውጭ ነበር። የሴቶችን ችግር በሩጉቲን መከራና ስቃይ ተጠቃለሉና የህሊናልጣንን ኃይል ዘግኘቱ ተመሳሰሉ በቀረዘበት፣ ሰሰው ደግ እሠራለሁ ሠግሱ እንደገና እስር ዜት እንዲገባ ዘተወሰነበትና በዚህም የተነሣ እድግ ዘተማረረበት ውትት ነበረ ክዜትን ያገኛት። ምናልባትም እኚያ ሕይወቱን የሰጠቡት ቋጳስ ትዝታ በመነመነበትና «እንደገና ተመልሰህ ወደ ተንኮል፣ ክፉትና ምቀኝነት ጉሮ ተመለስ» የሚል ስሜት ሕሊናው ውስጥ ዘተቀረጸበት ሰዎን ሊሆን ይችላል ክዜትን ያገኛት። በዚህ ወትት ነው ፍትር በድንገት ብቅ ብሎ ሕይወቱን እንደገና የለወጠውና የመንፈስ ኃይል የተገናጸፈው። ከዜት ይበልጥ ጉልበትና አትም ስለነበረው ክዜትን ጠበቃት፣ ተንከባከባት። እርስዋም የበለጠ ብርታት አገናጸፈችው። ምስጋና ለዣን ቫልዣ ይሁንና እርስዋም ቁም ነገሳ መራመድ ቻለች። ምስጋና ለእርስዋም ይሁንና ሕይወቱን ከፉና ጎዳና እንዲያስገባ አደረገችው። እርሱ እንደደገፋትና እንደረዳት ሁሉ እርስዋም ደገፈችው፣ ረዳችው።

❁❁❁

፪

እነዣን ቫልዣ ከነበሩበት አካባቢ ከዙተከርስተይን ደጃፍ የማይጠፋ አንድ ለማኝ ነበር። ዣን ቫልዣ በዚያ ባለፈ ቁጥር ሣንቲም ይጥልለታል። ለማኙን የሚመቀኙ የመንደሩ ሰዎች ሰላይ ነው እያሉ ያወሩበታል። አልፎ አልፎ ዣን ቫልዣ ቆም እያለ ያዋራዋል። ግን ሲያዋራው ለማኙ ቀና አይልም።

አንድ ቀን ማታ ዣን ቫልዣ በዚያ ሲያልፍ ለማኙ ዘመትር ስሚቀመጥበት ቁጭ ብሎ ያየዋል። ያን እለት ክዜት አብራው አልነበረችም። ስውዬው ከተቀመጠበት አጠንብ የመንገድ መብራት በርቶ ስለነበር በግልህ ይታያል። ዣን ቫልዣ እንደተለመደው ወደ እርሱ ሄዶ ሣንቲም ሰጠው። ለማኙ ቀና ብሎ በማየት አፈጠጠበት። ወዲያው ወደ መሬት አቀረቀረ። የሰውዬው አመለካከት ቅጽበታዊ ስለነበር ዣን ቫልዣን አስደንገጠው። ፊቱን ሲያየው ያ ዘመትር ጉብጦ እና የሰባ ዓመት ሽማግሌ መስሎ ይቀመጥ የነበረው ሰው ቱደም ሲል የሚያውቀውና የሚከታተለው ከፉ ሰው እንደሆነ ጠረጠረ። በዚህ ጊዜ ጥቅጥቅ ካለ ጫካ ጉበር ያሃ መሰለው። ማናዥ ወይም መሮጥ ወይም ሠቆም ተሳነው። ለማኙን አተኩሮ ከማየት ግን አልቦዘነም።

«ወይ ጉድ!» አለ ጎን ቫልዣ እርስ በራሱ ሲነጋገር። «አበድኩ፣ በሕልሜ መሆን አለበት! ሊሆን አይችልም!» አለ እየተጨነቀና እየተከዘ ወደ ቤቱ ተመልሶ ሄደ። ያየው ለማኝ ጎቭሮር እንደሆነ ራሱም ማመን አቃተው። ትገርት እንጂ እውነት አይሆንም ሲል ደመደመ።

ያን አለት ማታ ያየው ሰው ጎቭሮር እንደሆነ ለማወቅ እንዲችል ስላላናገረው በጣም ቆጨው። በሚቀጥለው ቀን ለዓይን ያዝ ሲያደርግ ወደዚያ ሥፍራ ሄደ። ለማኙ ከተለመደው ሥፍራ ጸሎት የሚያደርስ መስሎ ቁጭ ብሎአል። እንደተለመደው ሣንቲም እየጣለለት «ታዲያስ ደህና አመሸህ» ሲል ሰላምታ ሰጠው። ለማኙ «እግዚአብሔር ይስጥልኝ፣ ያሰንብትልኝ» ብሎ መልስ ከሰጠ በኋላ መፅዋቾቹን ለማየት አሠጉንም ቀና አለ። እውነትም ጠዋሪ ያጣ የሸማግሌ ለማኝ እንጂ ጎቭሮር እንዳልነበረ አረጋገጠ።

«እኔስ ምን ማለቴ ነው? አሁን ጎቭሮር ከየት መጣ ብዬ አሰብኩ? ወይ ጉድ! ዓይኔ እየደከመ ነው?» በማለት ካሰላሰለ በኋላ ነገሩን ረሳው።

ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ ከምሽቱ ወደ ሁለት ሰዓት ገደማ ይሆናል፣ ከክፍሉ ውስጥ ክዜትን የእጅ ጽሑፍ እያለማመደ ሳለ የቤቱ ዋና መግቢያ ያለውትሮው ተከፍቶ ሲዘጋ ሰማ። እንግዳ ነገር ሆነበት። ከቤቱ ውስጥ የሚኖሩት እሱ ራሱ፣ ክዜትና አሮጊትዋ ናቸው። አሮጊትዋ እንደሆነ ሽማ ለመቆጠብ ስትል ገና ሳይጨልም ነው የምትተኛው። ክዜት ገዘም እንድትል ምልክት ሰጣት። በደረጃው ሰው ለመውጣቱ ኩቴ ሰማ። ምናልባት አሮጊትዋ ትሆናለች ሲል አሰበ። አሁንም አዳመጠ። ከበድ ያለ ኩቴ ስለነበረ ዋወንድ ኩቴ መሰለው። ግን አሮጊትዋ የምትጠቀምበት መጫሚያ እኮ በጣም ከባድ ነው። ሆነም ቀረም ጎን ቫልዣ ሽማውን አጠፋ።

ክዜት እንድትተኛ ገፅ ባለ ድምፅ ከነገራት በኋላ ግምባርዋን ሳማት። የኩቴው ድምፅ ፀጥ አለ። ጎን ቫልዣ ከነበረበት ላይነቃነት ዝም ብሎ ከቆየ በኋላ ራቱን ወደ በር አዞረ። አካባቢው ፀጥ እንዳለ ጥቂት ጊዜ አለፈ። በበሩ የቁልፍ ቀዳዳ የሸማ መብራት ጭላንጭል አየ። በዚህም ከበሩ አካባቢ በውጭ በኩል አንድ ሰው ሽማ ይዞ እንደቆመ አረጋገጠ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በቁልፉ ቀዳዳ ይታይ ይነበረው ጭላንጭል ጠፋ፣ ግን ኩቴ አልተሰማም። ጎን ቫልዣ ልብሱን ሳያወልት ከአልጋው ላይ ተጋደመ። ሆኖም ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ አልወሰደውም።

ሲነጋ ሲል ትንሽ እንዳሸለበው በር ተከፍቶ ኖሮ በሩ ሲንጣጣ ቀሰቀሰው። ሌሊት የለማው ዓይነት ኩቴ ተንቀሳቀሰ። የኩቴው ድምፅ በመቃረቡ እየጮሳ ሄደ። ብድግ ብሎ ወደ በር በመሄድ በፀሩ ቁልፍ ቀዳዳ

ወደ ውጭ ተመለከተ። ሰፊ ቀዳዳ ስለነበር በደምብ ያሳያል። አንድ ሰው በጎን ቫልዣ ክፍል በራፍ አለፈ። በሩ አጠገብ ሲደርስ አልቆመም፣ ብዙ ብርሃን ስላልነበረ የሰውዬውን ማንነት ለመለየት አልቻለም። የሰውዬው ሙሉ ቁመና ከጀርባው ባየ ጊዜ በጣም ረጅም ሰው መሆኑን ተገነዘበ። ቅርጹንና የለበሰውን ልብስ ከጎቭሮር ጋር ሲያስተያየው ተመሳሰለበት።

የመስኮቱን መጋረጃ በመግለጥ በመስኮት ሰውዬውን ለማየት ፈልጎ ድፍረት ስላነሰው ተወው። ይህ ሰው በሩን በቁልፍ ከፍቶ እንደገባ አልተጠራጠረም። ታዲያ የበሩን ቁልፍ ማን ሰጠው? ምንድነው ነገሩ?

ከጠዋቱ በአንድ ሰዓት መቶ ፍራንክ ከቦርሳው አውጥቶ ካጣጠፈው በኋላ ኪሱ ውስጥ ጨመረው። እጁን ከኪሱ ሲያወጣ ሣንቲሞች ከኪሱ ሾልከው መሬት በመውደቃቸው አስደነገጡት። ወደ ምድር ቤት ወርዶ በድብቅ ውጭውን ተመለከተ። ጭር ብሏል፣ ማንም በዚያ አካባቢ አይታይም። ሆኖም በአካባቢው ብዙ ዛፎች ስለነበሩ ማን እንደተደበቀ ለማየት አይቻልም። ወደ ክፍሉ ተመለሰ። «ክዜት ተነሽ» አለ። እጅዋን ይዞ ተያይዘው ከቤታቸው ወጡ።

❁❁❁

ምዕራፍ አሥራ አንድ

በጨለማ የሚሸፍት ድምፅ-የለሽ ውሻ

ጎን ቫልዣ ዋናውን መንገድ ትቶ በመንደር ውስጥ ተጓዘ። መንደር ውስጥ የሚታጠፍ መንገድ ካጋጠመው ቀጥታውን ትቶ ይታጠፋል። ይህንንም ያደረገው ምናልባት የሚከተለው ሰው ካለ ዱካውን ለማጥፋት ነበር።

ጨረቃዋ ሙሉ ነበረች። ይህም በመሆኑ ጎን ቫልዣ ደስ አለው። የጨረቃው ብርሃን ሁሉንም ያሳይ ስለነበረ በተለይ ራት ብሎ ሲሄድ ሰው እንዳልተከተለው አረጋገጠ። ከምሽቱ አምስት ሰዓት ገደማ በፓኖ ፖሊስ ጣቢያ አጠገብ አለፈ። አጣቢያው ጥቂት እንደራቀ ማጅራቱን ከበደው። ራቱን ወደኋላ አዙሮ ተመለከተ። የጣቢው መብራት ወገግ ብሎ ይበራ ስለነበር ሦስት ሰዎች እንደሚከተሉት ተገነዘበ።

«ትንሽ ፈጠን በይ ልጅ» አላት ክዜትን። ክዜያ አካባቢ ቶሎ ለመዋፋት አርስም ፈጠን አለ። ጥቂት እንደተጓዙ ከአደባባይ ደረሱ። ጨረቃዋ ከፍ

በማለትዋ የአደባባዩ አካባቢ ወሰል ብሎአል። እነዚያ ሦስት ሰዎች እነማን እንደሆኑ ለማወቅ ዣን ቫልዣ ጨለምለም ካለ ከአንድ በር አጠገብ ተሸጉጠ። ብርሃን ስለነበር ሰዎቹ በአደባባዩ ሲያልፉ ሊያያቸው ይችላል። ሰዎቹ ጊዜ አልወሰዱም፤ ወዲያው ከአደባባዩ ደረሱ። አሁን አንድ ሰው ተጨምሮ አራት ሆኑ። አራቱም ዱላ ይዘዋል። ሁሉም ግዙፍ ሰውነት ስለነበራቸው በጣም ያስፈራሉ።

ከአደባባዩ ሲደርሱ ቶም ብለው ይወያዩ ጀመር። ከመካከላቸው አንዱ መሪያቸው ሳይሆን አልቀረም፤ ዣን ቫልዣ ወደሔደበት አቅጣጫ አመለከተ። ሌላው ደግሞ ወደ ሌላው አቅጣጫ በጣቱ በመጠንቀር አሳየ። የቡድኑ መሪ ወደ አመለከተበት አቅጣጫ ፊቱን ሲያዞር የጨለፈቃ ብርሃን ከፊቱ ላይ በግረፋ በግልጽ ታየ። መሪው ዣቨር እንደነበር ዣን ቫልዣ አወቀው።

«ወዴት ይሄድ ይሆን!» ሲል ዣን ቫልዣ አሰበ። ሰዎቹ ቆመው ሲከራከሩ እርሱ ለማምለጥ ፈልጎ ከተደበቀበት መጥቶ ላይታይ በእቋራጭ መንገዱን ተጠለ። መንገዱ ላይ ሰው አልነበረም። ፊጠን፤ ፊጠን አለ። ወደኋላ ዞር ብሎ ተመለከተ። ማንም የለም።

ድልድይ ካለበት ደረሰ። አንድ ትልቅ እቃ የተጫነ ጋሪ ድልድዩን ቀስ ብሎ ሲያቋርጥ አየ። ጋሪው እርሱ ወደሚሄድበት አቅጣጫ ነበር የሚሄደው። ጋሪውን ነሰላ በማድረግ መንገዱን ተጠለ። ጥቂት ከተጓዘ በኋላ ፊቱን አዙሮ ወደኋላ ተመለከተ። ከሩቁ የአራት ሰዎች ጥላ አየ። ሰዎቹ ግን በአካል አልታዩትም።

አዳኝ እንደደረሰባት ድኩላ ሰውነቱ ተረበሸ፤ ተስፋው መነመነ። ብዙ ዛፍ ከነበረበት ሜዳ ከደረሰና መንገዱን ካነበረ እንደሚያመልጣቸው ያውቃል። ከአንድ ቀጭን መንገድ ስለደረሰ በዚያ ታጥፎ ሩጫውን ተጠለ። ጥቂት እንደተጓዘ ከመንታ መንገድ ደረሰ። ወደቀኝ ይታጠፍ ወይስ ወደ ግራ! አላወላወለም፤ ወደ ቀኝ ታጠፈ።

ለምን?

ምክንያቱም ወደ ግራ የሚታጠፈው መንገድ ነዋሪ ወደሌለበት ወደ ገጠር ነበር የሚወስደው።

አልፎ አልፎ ወደኋላ እየነረ ያያል። ሁልጊዜም የሚጓዘው ብዙ ብርሃን የሌለበትንና ጨለምለም ያለውን መርጦ ነው። ከኋላ ትቡት የመጣው መንገድ ቀጥ ያለ ነበር። ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ወደኋላ ዞሮ ሲያይ ማንም አልተከተለውም። ምድሪቱ አሁንም ጸጥ እንዳለች ናት። ትንሽ ተንፈስ አለ፤ ጉዞውን ግን አላቆመም። ጥቂት እንደተጓዘ አሁንም ፊቱን

ቢያነሣ በሩቁ የሚንቀሳቀስ ነገር ያየ መሰለው።

ፊጠን፤ ፊጠን ብሎ በመሄድ የማታጠፍ መንገድ ፈለገ። የሚከተሉትን ሰዎች ለማሳሳት ነበር። አንድ ትልቅ ግንብ ካለበት ደረሰ። የተገነበት ጠባብ መንገድ ግንብ ከነበረበት ሲደርስ አለቀ። የግንቡን ጥግ ይዞ ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ ማለፍ ይቻላል። አሁንም ዣን ቫልዣ መወሰን ነበረበት፤ ወደ ቀኝ ወይስ ወደ ግራ?

ወደ ቀኝ ተመለከተ። በሩቁ ጠበብ ያለ ጉዳና ታየው። ከመንገዱ ሻገር ከነበሩ ሮት ቤቶች አጠገብ ያሉት ዛፎች መሸሸጊያ ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚያ ቢደርስ ራሱን ለመደበት የሚችል መሰለው።

ኩሎሞኑ መንገድ ሲደርስ አሁንም መንገዱ ለሁለት ተከፈለ። ወደግራ ሊመለከት አንድ ትልቅ ነጭ ተለም የተቀባ የግንብ አጥር አየ። ግንቡ ወደ ሁለት መቶ አርምጃ ቢርቅ ነው። ግራው መንገድ የሚሻል መሰለው።

ወደ ግራ ለመታጠፍ እንደወሰነ አንድ ሀውልት ወይም ሰው መሆኑ የሚያጠራጥር ነገር በሩቁ አየ። እርሱን ለመከታተል ትእዛዝ ደርሶት የሚጠባበቅ ሰው መሰለው። ዣን ቫልዣ ደነገጠ። መንገዱን ዘግቶ ሰው እንደሚጠብቀው ተረዳ።

ምን ይሻላል?

ወደ ኋላ ለመመለስ ጊዜ የለም። ዣቨር ከነሠራዊቱ ቶሎ ደርሶ እንደሚይዘው ጠረጠረ። ምናልባትም ተቃርቦዋል። እስካሁንም ያንተተው የመንገዱ ጠመዝማዛነት ና መከፋፈል ሊሆን ይችላል። ፖሊስ እንደመሆኑ መጠን መግቢያ መውጫውን በሚገባ ያውቀዋል። በየማለፊያው ሰው አስቀምጦ ይሆናል። ወደ ሰማይ የተቡተነ አዋራ ወደየአቅጣጫው እንደሚተን ሁሉ የዣን ቫልዣም አሳብ እንዲሁ ተቡተነ። ወደፊት መራመድ ማለት ቶሞ ከሚጠብቀው ሰው እጅ መውደት ማለት ሆነ። ወደኋላ መመለስ ማለት ደግሞ ከዣቨር እጅ መግባት ነው። ዣን ቫልዣ ቀስ በቀስ በሚጠመጠም ሰንሰለት የተጠፈረ መሰለው። ተስፋ በመቁረጥ ወደ ሰማይ አንጋጠጠ።

❄❄❄

ፔጫታ ከሩቁ ተሰማ። ዣን ቫልዣ አንዱን ቤት ተጠግቶ ለመደበቅ ፈለገ። ከሩቅ የሚንቀሳቀስ ጥላ ተመለከተ። ሰዎች ወደ እርሱ ማምራታቸውን

ተገነዘበ። ተንጠላጥሎ ድምፅ ወደሚሰማበት አቅጣጫ ተመለከተ። የዣቭርን ግዙፍ ሰውነት መለየት አላዳገተውም። በፖሊስ ጥንቃቄ ግራና ቀኝ እያየ መራመዳቸውን ተመለከተ። ቆም እያሉ፣ አካባቢውን እየሰለሉ ነው የሚሄዱት። የመደበቂያ ሥፍራ እንዳለ አጥርተው እንደሚፈትሹ ያስታውቃል። ሰፈሩ ማምለጫ መንገድ የለውም።

በዚያ አካሄዳቸው ሥፍራውን እየፈተሹ ሲመጡ ዣን ቫልዣ ከነበረበት ለመድረስ ምናልባት ሩብ ሰዓት ቢወስድባቸው ነው። እጅግ በጣም የሚያስጨንቅ ሰዓት ነበር። በሕይወቱ ዘመን ለሦስተኛ ጊዜ ከአስፈሪ ሕይወት ጫፍ ላይ የደረሰ መሰለው። አሁን ያስፈኔነቀው የእስር ቤት ኑሮ ብቻ ላይሆን የከዜት ከእርሱ መለየት ጭምር ነበር። ሁለት አማራጭ ነበረው፤ የመለኮት ኃይል አውጣኝ ብሎ መማጠን ወይም ባለው ጉልበት ተጠቅሞ ለወቼን መጋፈጥ።

እስር ቤት ባገኘው ልምድ ዣን ቫልዣ ቀጥ ካለ ግንብ፣ ቁመቱ እንደ ፈለገው ቢረዝም እንኳን፣ በቀላሉ የመውጣት ችሎታ አለው። ከፊት ለፊቱ የነበረውን ግንብ ርዝማኔ በዓይኑ መተረው። ወደ አምስት ሜትር ገደማ ይሆናል። በተጠረበ ድንጋይ የተሠራ ግንብ ነበር።

አሁን የምታስቸግረው ከዜት ስትሆን ከዜት ከግንብ ላይ መውጣት አታውቅበትም። ታዲያ ይተዋት? አላቡ አንገሸገሸው። እርስዋን ተሸክሞ መውጣት ደግሞ የማይቻል ነው።

መፍትሔው ትልቅ ገመድ እንደሆነ ተገነዘበ። ግን ዣን ቫልዣ ገመድ አልነበረውም። ታዲያ ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ገመድ ከየት ሊያመጣ ይችላል? በዚያች ሰዓት ዣን ቫልዣ አገረ ገዥ ቢሆን ግዛቱን በአንድ ወፍራምና ረጅም ገመድ ይለውጥ ነበር።

የሚደንቀው አንዳንድ ጊዜ በጭንቀት ሰዓት የሚያስገርም ወይም ለማመን የሚያስቸግር ነገር ይሆናል። ዣን ቫልዣ ግራና ቀኙን ሲቃኝ መብራት የተንጠለጠለበት ገመድ አየ። በዚያን ጊዜ እንደዛሬ የኮረንቲ ብርሃን ባልነበረበት ዘመን በጋዝ የሚሠሩ መብራቶች ከፍ አድርገው የሚሰቅሉትና የሚያወርዱት በወፍራምና በረጅም ገመድ ነበር።

ዣን ቫልዣ ገመዱ ወደ ተንጠለጠለበት ርጦ በያዘው ቢላዋ ቆረጠው። ቀደም ሲል እንደተገለጸው በተለይ ያን ምሽት ፈኔረቃዋ ሙሉ ስለነበረች የመንገድ መብራቶች አልተለኮሱም። ስለዚህ ዣን ቫልዣ ገመዱን ሲቆርጥ ምናልባት መብራቱ ቢሰበር ልብ የሚለው አልነበረም። አካባቢውም ጭር ያለ ነበር።

ዣን ቫልዣ ከወዲህ ወዲያ ሲሮጥ፤ ዓይኑ ሲቅበዘበዝ አላብ ሲያስጨንቀው በማየትዋ ከዜት ደነገጠች። እርስዋ በመሆንዋ እንጂ ሌላ ልጅ ብትሆንማ ልቅሶዋን ነበር የምትለቅቀው። የኩቱን ጭራ አጥብቃ ይዛ ዝም ብላ ነበር የምትከተለው። በአካባቢው የሚሰማው ድምፅ እየጎላ መጣ።

«አባባ» አለች ከዜት በጣም ዝቅ ባለ ድምፅ፤ «ፈራሁ፤ ማነው የመጣው?»

«ዝም በይ፤ ዝም በይ» አለ የተከፋው ሰው፤ «ሚስስ ቴናድዬ ናት።»

የከዜት ሰውነት በፍርሃት ተንቀጠቀጠ፤ ሰውዬው ንግግሩን ቀጠለ።

«አይዞሽ እኔ አለሁልሽ፤ ግን ዝም ነው፤ ካለቀስሽ ወይም ድምፅ ካሰማሽ ሚስስ ቴናድዬ ትሰማሻለች። አንቺን ፍለጋ ነው የመጣችው።»

ዣቭርና ሌሎች ፖሊሶች እነርሱ ከነበሩበት ደርሰው ሊይዟቸው ከመቻሉ ጊዜ ማባከኑ ይብልጥ የሚያጋልጥ መሆኑን ተገነዘበ። ከረባቱን አውልቆ በከረባቱ የከዜትን ወገብ አሰረ። ጫማውንና ካልሲውን አውልቆ ከግንቡ ላይ ወረወረ። የገመዱን አንዱን ጫፍ ከቋጠረ በኋላ ከከዜት ወገብ ላይ ከታሠረው ከረባት ጋር አሰረው። ከዚያ በኋላ የገመዱን አንድ ጫፍ በአፉ ይዞ ከግንቡ ላይ መውጣት ጀመረ። ከዜት ከመሬት ሆና ዝም ብላ ታየዋለች። የሚስስ ቴናድዬ ስም በመጠቀሱ በጣም ስለደነገጠች ለመናገር ብትፈልግ አንኳን መናገር አትችልም።

ብዙ አልቆየም ወዲያው እጅግ ዝቅ ባለ ድምፅ ዣን ቫልዣ ሲጠራት ሰማች።

«ጆርባሽን ለግድግዳ ስጪ።»

እንዳዘዛት አደረገች።

«እንዳት-ናገሪ፤ እንዳት-ፊሪ» አለ ዣን ቫልዣ ቀጠሉና።

መሬት ለቅቃ ስትንጠለጠል ታወቃት። የት እንዳለች ላታውቅ ትንሽ ጫፍ ደረሰች። ወዲያው ዣን ቫልዣ እቅፍ አደረገና በጀርባው አዘላት። እጆችዋን በግራ እጁ ያዘ። እንደገመተው ከግንቡ ኋላ ቤቶች ነበሩ። ቤውስዮ በከፉ የግንቡ ርቀት እስከዚህም ሩቅ አልነበረም። ርቀቱን በሳይኑ መተረው።

ልጅትዋን እንዳዘለ በቀላሉ ከአንድ ቤት ጣራ ላይ ለማረፍ ቻለ። ከዚ ሆኖ ከአጥሩ ውጭ የዣቭርን ድምፅ ሰማ።

«በየመንገዱ፣ በየሥርቻው ቶሎ ብላችሁ ፈልጉት። በየቢሮ
እየገባችሁ ፈልጉ። ስለሚደርስው ነገር እኔ አልፋለሁ» አለ ጎርዜር እየጮ

ጎን ቫልጎ ከጣራው ላይ ቁጭ አለ። ኮዜትን በገመዱ አንጠልጥ
የዛፍ ግንድ ይዛ በመውረድ መራት አስከትደርስ ጠበቃት። ኮዜት ጎ
ይሁን ፈርታ ቃል አልተነፈሰችም። እጅዋን ሲጨብጣት ግን በጣም አልቡ
ነበር።

ጎን ቫልጎ ከጣራ ወርዶ ሲጓዝ ከአንድ የአትክልት ቦታ ደረ
አካባቢው በጣም ጭር ያለ ነበር። በመጀመሪያ ጫማውንና ካልሲው
መፈለግ ነበረበት። ጫማውን ፈልጎ ካጠለቀ በኋላ ከኮዜት ጋር ከዛፍ
ስር ተቀመጡ። ምንጊዜም ቢሆን የሚሸሽ ሰው ያመለጠ ስለማይመስ
ሁልጊዜም እንደ ደነገጠ ነው። ኮዜት ስለፈራች ከጎኑ ተሸጉጠች። እነዣቭ
ሲጠራሩ አሁንም ይሰማል። ግን ከሩብ ሰዓት በኋላ ድምፁ እየደከመ ሄ
ቢሆንም የጎን ቫልጎ ልብ አሁንም አልረጋም። ኮዜትም ዝምታዋን ቀጠለች

ከዚህ መጣ የማይባል ድምፅ በድንገት ተሰማ። የደናግል ገመ
ነበር። ደናግል ተሰባስበው የሚዘምሩት አትክልት ውስጥ ነበር። ድም
ጥርት ብሎ ነው የሚሰማው። ጎን ቫልጎ ይህን ድምፅ ሲሰማ የድምፁ
አትጣጪ ፍለጋ ዞር አለ።

ፊቱን ሲያዞር ከአትክልቱ ውስጥ ሰው መኖሩን አየ። አንድ ሰ
ጎንበስ ቀና ይላል። ሰውዬው ሥራ ይዞ መሆን አለበት፤ እቃ ከአን
ሥፍራ አንስቶ ወደ ሌላ ቦታ እንደሚወስድ ሰው ጎንበስ ይልና ቀና ብ
ጥቂት ይራመዳል። ተመልሶ መጥቶ ጎንበስ ይልና ቀና ብሎ ይሄዳል።

ጎን ቫልጎ ደነገጠ። ምናልባት ጎቨርና ተከታዮቹ እዚህም ጠ
ያስቀመጡ መሰለው። ይህ ሰው የእነርሱ አባል ከሆነ «ሌባ፣ ሌባ» እ
ቢያሲዘኝስ ሲል አሰበ። የተኛችውን ኮዜት ቀስ ብሎ አንስቶ ግቢው ው
ከነበረው አሮጌ አግዳሚ መቀመጫ ላይ አሳረፋት። ኮዜት አልነቃችም።

ከኮዜት አጠገብ ተቀምጦ የሰውዬውን እንቅስቃሴ ተከታተለ
የቃጭል ድምፅ ይሰማል። ሰውዬው አንድ ነገር ለማንሳት ጎንበስ ሲል
ቃጭሉ ሲቃጨል አኩል ስለመጣ ጎን ቫልጎ ይህ አጋጣሚ ይቀ
እንደሆነ ጠበቀ። አሁንም አኩል መጣ፣ ጨርሶ አልተዛባም። ሰውዬ
ሲንቀሳቀስ ቃጭሉ ድምፅ ያሰማል። ሲቆም ዝም ይላል። የሚደንቀ
ደግሞ ሰውዬው ሥራውን ጨርሶ ሲያርፍ ደወሉም ቦጥ ይላል። «የደመ
ገመድ ከሰውዬው ወገብ ላይ ታስሮ ይሆን?» ሲል አሰበ።

ይህን እያሰላሰለ የኮዜትን እጅ አሻሸ። አንደበረደ ተገነዘበ።

«ምን ይሻላል?» ሲል ራሱን ጠየቀ።

«ኮዜት» ሲል በለሰለሰ ድምፅ ጠራት።

ዓይንዋን አልገለጠችም። ቀስ ብሎ ወገብዋን ይዞ ነቀነቅ አደረጋት።
ከእንቅልፍዋ አልነቃ አለች።

«እንዴ፤ ይህቺ ልጅ ሕይወትዋ ከሥጋዋ ተለየ እንዴ?» ሲል
በድንጋጤ ከተቀመጠበት ብድግ አለ።

አልጋ ላይ እንደተኛ ሰው እግርዋን ዘርራ ነው የተኛችው። ትንፋሹዋን
አይመጠ፤ ተተነፍሳለች። ሕይወቱ መለስ አለች። ብርዱ ሊጎዳት እንደሚችል
ያውቃል። «ምን ላልብሳት? በምን ላማመቻት? በብርድ ልትሞት ነው»
ሲል አሰላሰለ። ከነበረበት ጥቂት ተራምዶ ከሥፍራው ፈቀቅ አለ። የብርድ
ልብስ ያገኛ ይመስል ጎኑን ተቅበዘበዘ። በቶሎ ኮዜት ከቤት ውስጥ ገብታ
ቢቻል አሳት መሞቅ እንዳለባት አስተዋለ።

በቀጥታ ሲንቀሳቀስ ወዳየው ሰውዬ ሄደ። ከሰደርያው ኪስ ውስጥ
ጠቅልሎ ያስቀመጠውን ገንዘብ አወጣ። ሰውዬው አጎንብሶ ይሠራ ስለነበር
ወደ እርሱ የሚመጣውን ጎን ቫልጎን አላየውም። ጎን ቫልጎ ሰውዬው
ከነበረበት ደረሰ።

ጎን ቫልጎ ጠጋ ብሎ «መቶ ፍራንክ» ሲል ተናገረ። ሰውዬው
ደንግጦ ቀና አለ።

«ካሳደርከኝ መቶ ፍራንክ እከፍላለሁ» አለ ጎን ቫልጎ።

ከጎን ቫልጎ ፊት ላይ የጨረቃ ብርሃን አርፎ ነበር።

«እንዴ፤ አባታችን ማንደላይን፤ ከእዚህ ምን ትሠራለህ?» ሲል
ሰውዬው ጠየቀው።

በዚያ ጨለማ፤ በዚህ ባልታወቀ ቦታ፤ በዚህ በማይታወቅ ሰው ይህ
ስም ሲጠራ በመስማቱ ጎን ቫልጎ ወደኋላ ሸሸት አለ።

ሰውዬው ያጠለቀውን ቆብ ብድግ አደርጎ እጅ ነሳው።

«ቁጭ በል! ቁጭ በል! ቤት ለእንግዳ። ግን አባታችን እዚህ እንዴት
መጣህ? እንዴ፤ ደግሞ ከዚህ ግቢ ውስጥ እንዴት ልትገባ ቻልክ? ከሰማይ
ነው የወረድከው ወይስ ከምድር ነው የፈለቅከው?» ሲል በጥያቄ አጣደፈው።

«ማን ነምት እርስም? ቤቱስ የማነው?» ሲል ጎን ቫልጎ ሰውዬውን
ጠየቃቸው።

«በጣም ነው ደስ ያለኝ» አሉ ሽማግሌው። «እንተ እኮ ነህ ከዚህ

ያስገባኝኝ። ይህን ቤት ደግሞ አንተ ነህ ያስጠኝኝ። እንዴ! እንዴት ይሆናል፤ አታስታውሰኝም?»

«ይቅርታ፤ አላስታወስኩም» አለ ዣን ቫልዣ። «የት ነው የምንተዋወቀው?»

«ሕይወቴን እኮ አድነሃታል» አሉ ሰውዬው።

ዣን ቫልዣ አሁን ትዝ አለው። የሽማግሌውን ፊት አስተዋለ። እኚያ የጭንት ጋሪ ተጭኖዋቸው ሊሞቱ ሲሉ ከጋሪው እግር ፈልቅቆ ያወጣቸው ሰው መሆናቸውን አወቀ።

«ለካ እርስዎ ነዎት!» አለ ዣን ቫልዣ፤ «አሁን አስታወስኩ ሚስተር ፎሽለማ ነዎት፤ አይደለም?»

«ጥሩ አጋጣሚ ነው» አሉ ሽማግሌው።

«እርስዎስ ከዚህ ምን ይሠራሉ?» ሲል ዣን ቫልዣ ጠየቀ።

«ከዚህ ሥራ እየሠራሁ ነው፤ አንተስ ምን ትሠራለህ?» አሉ ቀጠሉና።

ዣን ቫልዣ በቀድሞ ስሙ እየጠራ የሚያናግረውና የሚያውቀው ሰው በማግኘቱ ጥቂት ተዝናና። የእንግዳ ዓይን አውጣ እንደ መጠየቅ እርሱ ጥያቄ ያበዛል።

«ጉልበትዎ ላይ ያሰሩት ደወል ምንድነው?»

«እሱማ» አሉ ሽማግሌው፤ «መምጣቴን አውቀው ከእኔ እንዲሸሹ ድምፅ የማሰማበት መሣሪያ ነው።»

«ከእኔ እንዲሸሹ?»

አምንታቸውን ለመግለጽ ሽማግሌው ግንባራቸውን ወደ ላይ ሰብ አደረጉ።

«ከዚህ ግቢ ውስጥ ያለው ከእኔ በስተቀር ሁሉም ሴት ነው። ውጣት ልጃገረዶች በብዛት አሉ። ከእኔ ጋር መገናኘቱ አደገኛ ነው መሰለኝ፤ ደወሉ ለመምጣቴ ማስጠንቀቂያ ነው። እኔ ስደርስ ይሸሻጋሉ።»

«ቤቱ የኔ ነው?»

«ምነው፤ ታውቀው የለም እንዴ?»

«የለም፤ አላውቀውም።»

«ምነው፤ አንተ አይደለህም እንዴ በአትክልተኝነት ተቀጥረህ እንድሠራ ያደረግኸው።»

«ለምጠይቀው ጥያቄ ምንም አያውቅም ብለው በመገመት መልስ ይስጡኝ።»

«አንተ ካልክ እሺ። ይህ ገዳም እኮ በዚያን ጊዜ የፐቲ ፔክፐስ ገዳም ነበር የሚባለው።»

ዣን ቫልዣ አስታወሰ። በአጋጣሚ ከሚያውቀው ገዳም መግባቱን ተገነዘበ። ከሁለት ዓመት በፊት ሽማግሌው የእቃ መጫኛ ጋሪ ወድቆባቸው ሳለ የአካል ጉዳት ስለደረሰባቸው በአትክልተኝነት ገዳሙ እንዲቀጥራቸው የድጋፍ ደብዳቤ ጽፎላቸው ነበር። የድጋፉ ደብዳቤ ነው እንዲቀጠሩ የረዳቸው።

«የፐቲ ፔክፐስ ገዳም» አለ ዣን ቫልዣ እርስ በራሱ ይነጋገር ይመስል።

«እንዴት አድርገህ ከዚህ ልትገባ እንደቻልክ ንገረኝ እንጂ፤ ሰው ስለሆንክ መልእክ ለመሆን አትችልም። በምንም መንገድ ደግሞ ወንድ ከዚህ ገዳም እንዲገባ አይፈቀድም።»

«ይኸው እርስዎ ከዚህ ይኖሩ የለ!»

«ያለ እኔ እኮ ሌላ ወንድ የለም።»

«ግን» አለ ዣን ቫልዣ «ከዚህ መኖር አለብኝ።»

«ያንተ አለህ!» ሲሉ ሚስተር ፎሽለማ በመደነቅ ዓይነት ተናገሩ።

ዣን ቫልዣ ወደ ሽማግሌው ጠጋ ብሎ ዝቅ ባለ ድምፅ «ምነው ሕይወትዎን ማዳኔን ረሱት?» አላቸው።

«መዘንጋት አልነበረብኝም» አሉ ሚስተር ፎሽለማ።

«እንግዲያውማ እኔ ለእርስዎ ያደረግሁትን ዛሬ እርስዎ ለእኔ ማድረግ ይኖርብዎታል።»

ፎሽለማ በተጨማደደ እጃቸው የሚንቀጠቀጠውን የዣን ቫልዣን እጅ ያዙ። ለጥቂት ሰኮንድ እጁን እንዲያዙ ዝም ብለው ቆሙ። በመጨረሻ፡-

«እኔ ለአንተ አንድ ነገር ማድረግ ከቻልኩ እግዚአብሔር ባረከኝ፤ ቃደሰኝ ማለት ነው። የአንተ ውለታ እኮ ተከፍሎ የሚያልቅ አይደለም። ሕይወትህን አድንልሃለሁ! ክቡር ከንቲባ፤ ሽማግሌው በአንተ ቁጥጥር ሥር ነው።»

ሽማግሌው ይህን ሲናገሩ በጣም ደስ እያላቸው ነበር። ለዚህ በመብቃታቸው መንፈላቸው ረካ። ለመደሰታቸው ፊታቸው መለከረ።

ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ?» አሉ ተጥለው።

«ግድ የለም አስረዳዎታለሁ። አንድ ክፍል አለዎት?»

«ከዚያ ጥግ አንዲት የማትረባ ክፍል አለች። ግን ሰው የሚኖርባትም እትመስል። እኔ ያለሁበት ቤት ባለ ሦስት ክፍል ነው።»

እውነትም የሰውዬው ቤት የማይረባ ዝቅተኛ ቤት ነበር። አቀማመጡም ሆን ብሎ ሰው ለመደበቂያ የተሠራ ይመስል ከአሳቻ ሥፍራ ነበር። ዣን ቫልዣ ከግቢው ውስጥ ሲገባ ያልታየው በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

«ጥሩ ነው» አለ ዣን ቫልዣ፤ «አሁን ሁለት ነገር ነው የምጠይቅዎት።

«ምንና ምን ናቸው ክቡር ከንቲባ። ብቻ እርስዎ አያልኝ፣ ባትጠራኝ።

«እሺ! እንደኛ፤ አሁን ስለራሴ የምነግርህን ለማንም እንዳታወራ ሁለተኛ እኔ ከምነግርህ ውጭ ስለእኔ ለማወቅ እንዳትሞክር።»

«አንተን ደስ እንዳለህ። አሳፋሪ ነገር የማትሠራና የእግዚአብሔር ሰው እንደሆንክ አውቃለሁ። ከዚህም በላይ ከዚህ አንድትገባ የረዳኸኝ አንተ ስለሆንክ ቤትህ ነው። እኔም ያንተ ነኝ።»

«በጣም ጥሩ፤ ና አሁን ተከተለኝ፤ ልጅትዋን እናምጣት።»

«እንዴ» አሉ ፎሽለማ በመገረም። «ልጅም አለች!»

ውሻ ጌታዋን ተከትላ እንደምትሄድ፤ ሰውዬው ሌላ ቃል ሳይናገ ዣን ቫልዣን ተከትለው ወጡ።

ከግማሽ ሰዓት በኋላ አሳት ተቀጣጥሎ ከዚት አሳት ትሞት ጀመር ሽማግሌው ከዚትን አልጋ ላይ አስተኝዋት። ዣን ቫልዣ ወደ ግቢ ወርውሮአቸው የነበሩትን እቃዎቹን አግኝቶ ተመለሰ። ሽማግሌው ከንልበታቸው ላይ ያሠሩትን ቃጭል ፈትተው አስቀመጡ። ሁለቱ ሽማግሌዎች እራት እየበሉ ፊጌዎታ ቀጠሉ።

«የሚገርም ነው ክቡር ከንቲባ። በመጀመሪያ አላወትኝኸኝም፤ ለምን ሕይወታቸውን ነዳንክላቸው በኋላ ትረሳቸዋለህ? ይኸ ደግ አይደለም እነርሱ ግን አያረሱህም። የምትረሳ ሰው አይደለህም።»

ምዕራፍ አሥራ ሁለት

ገዳመ.

ዣን ቫልዣ ለመተኛት ዓይኑን ከመጨፈኑ በፊት «ከዛሬ ጀምሮ ከዚህ እናራለሁ» ሲል ተናገረ። እነዚህ ቃላት የሚስተር ፎሽለማን ጭንቅላት ሲከብቡት አደሩ። ሁለቱም እንቅልፍ ሳይወስዳቸው ነው ያደሩት። ዣቨር ፍለጋውን እንደሚያጧጥፍ ዣን ቫልዣ ያውቃል። ከዜትና ዣን ቫልዣ ወደ ከተማ የተመለሱ እንደሆነ ይያዛሉ። ስለዚህ ከገዳሙ ውስጥ መቆየት እንደሚሻል ዣን ቫልዣ አመነ። ሆኖም ለመደበቅ የሚያመች ሥፍራ ቢሆንም ወንድ ከዚያ ስለማይገባ አደገኛ ነው። ከገዳሙ ውስጥ መኖሩ ከታወቀ በወንጀል ተከስሶ ይታሰራል።

ሚስተር ፎሽለማ ደግሞ ስለነገሩ ግራ ገብቷቸው ስለተጨነቁ እንቅልፍ አልወሰዳቸውም። «እንዴት ከንቲባው ከዚያ ሊገባ ቻለ? ገዳሙ ዙሪያውን በግንብ አጥር በመታጠሩ ሰው ከዚያ ሊገባ አይችልም። ልጅትዋን ከየት አመጣት? ማንም ቢሆን ልጅ አገዛሎ ከግንብ ላይ ሊወጣ አይችልም። ልጅት የስ የማን ልጅ ናት? ከየት ነው የመጡት? ምናልባት ገንዘብ አጉድሎ እየሸሸ ይሆን? ወይስ በፖለቲካ ጉዳይ እየተፈለገ ነው?» ሲሉ ሽማግሌው ራሳቸውን ጠየቁ። «ምናልባት ገዳሙን የመረጠው ጥሩ የመደበቂያ ሥፍራ ስለሆነ ይሆን?» ሲሉም አሰቡ።

«መሴይ ማንደላይን ከሞት ያዳነኝ ሰው ስለሆነ አሁን የእኔ ተራ ነው» በማለት ዣን ቫልዣን ለመርዳት ወሰኑ።

«ለሕይወቱ ሳይሳሳ ያንን የሚያህል ጭንት ከጫነው ጋሪ ስር ገብቶ ነው ሕይወቴን ያዳናት! ግን እርሱን ከዚህ ማናር ወንጀል ነው። ብያዝ ምን አመልሳለሁ?» ሲሉ ተጨነቁ።

ሽማግሌው አስከዚህም ለሰው የሚጨነቁና ይሉኝታ የሚያጠቃቸው ሰው አልነበሩም። አሁን ግን በእድሜም እያረጁ ስለሄዱ ፤በስተእርጅና ሰው ላይ ምን አስጨከነኝ፤ የሚል ስሜት ተሰማቸው። የአካል ጉዳት ደርሶባቸው ገዳም ውስጥ ለሁለት ዓመት ስለኖሩ ስለሕይወት የነበራቸው አመለካከት ሳይለወጥ አልቀረም። በመጨረሻ ሕይወታቸውን ለመሴይ ማንደላይን ለመሰዋት ወሰኑ።

ሚስተር ፎሽለማ ቀስ ብለው በር ሲያንኳኩ «ይግቡ» የሚል መልስ አገኙ። የገዳሙ ኃላፊም ቢሮ ነበር። ክቢሮው እንደገቡ ለቮ ብለው እጅ

«እርስዎ ነዎት እንዴ አባታችን::»

እንደገና ለጥ ብለው እጅ ነሱ::

«እኔ ነኝ ያስጠራሁዎት::»

«በጥሪው መሠረት መጥቻለሁ::»

«ለምን ነበር እኔን ለማነጋገር የፈለጉት?»

«ጉዳይ ነበረኝ::»

«የምን ጉዳይ?»

ሚስተር ፎሽለማ ለሁለት ዓመት ገዳሙ ውስጥ ሲኖሩ ከተማው ውስጥ የሚነገረውን ሁሉ ይሰማሉ:: ግን የሰሙትን ሁሉ የመደበቅ ችሎታ ነበራቸው:: የገዳሙ ነዋሪ እንደቂል ነበር የሚያያቸው:: ሴሮች ግን በጣም ያከብሯቸዋል:: ሹማግሌው ስለሥራቸው ስፋት ለሴሮች ኃላፊ ብዙ አወሩ:: ቀኑ አልበቃ ብሏቸው ሌሊቱን ሁሉ በጨረቃ ብርሃን እንደሚሠሩም ለኃላፊዋ ከገለጹ በኋላ አንድ ወንድም እንዳላቸውና እርሱም ከእርሳቸው በእድሜ ይነስ እንጂ ልጅ አለመሆኑን አስረዱ:: ወንድማቸው ከእርሳቸው ጋር እንዲኖር ቢፈቀድላቸው በሥራ ብዙ ሊረዳቸው እንደሚችል ሲናገሩ የኃላፊዋ ሰውነት ተሸማቀቀ::

ሹማግሌው ንግግራቸውን በመቀጠል ወንድማቸው ጎበዝ አትክልተኛ መሆኑንና እርሱ ካልረዳቸው በእድሜ ምክንያት ሥራው ስለሚከብዳቸው ምናልባት ሥራውን ለመልቀቅ እንደሚገደዱ ተናገሩ:: በተጨማሪም ወንድማቸው ትንሽ ሌት ልጅ እንዳለውና ከእርሳቸው ጋር እንዲኖር ከተፈቀደላቸው ልጅትዋ በሃይማኖት ተኮትኩታ ልታድግ እንደምትችል ገለጹ:: ምናልባት አንድ ቀን ይህቺ ልጅ መንኩሳ ቤተክርስቲያንን ልታገለግል እንደምትችልም አስረዱ::

ሹማግሌው እንደጨረሱ ኃላፊዋ መነኩሲት ሥራ እንዲሠሩ አዘዝዋቸው::

«እስከ ነገ ማታ አንድ ወፍራም ብረት ሊገዙልኝ ይችላሉ?»

«ለምን ሥራ?»

«ለአንድ ሥራ::»

«ምን ገድደኝ! እችላለሁ እንጂ!» ሲሉ መለሱ ሹማግሌው:: ኃላፊዋ መነኩሲት ይህን ተናግረው ወጥተው ሄዱ:: ፎሽለማ ብቻቸውን ቀሩ::

አንድ ሩብ ሰዓት አለፈ:: ኃላፊዋ ሴር ተመልሰው ከመቀመጫቸው ተቀመጡ:: ሁለቱም አሳብ የያዛቸው መሰሉ::

«አባታችን?»

«አማሆይ!»

«የጸሎት ቤቱን ያውቁታል?»

«ለቅዳሴ አልፎ አልፎ ወደዚያ ስለምሄድ አውቀዋለሁ::»

«ከዚያ ይሄዳሉዋ?»

«ከአንዱም ሁለቱ፤ ከሁለቱም ሦስቱ ሄጃለሁ::»

«ከዚያ የሚፈነቀል ትልቅ ድንጋይ አለ::»

«ከባድ ነው?»

«የሚፈነቀለው ድንጋይ ያለው ከቤተመቅደሱ አጠገብ ነው::»

«ብዙ ቦታ ከሆነ አንድ ሰው ብቻውን መፈንቀል አይችልም:: ሁለት ወንዶች ያስፈልጋሉ::»

«ከመነኩሳቱ መካከል አራቱ ይረዱዎታል::»

«ይኸው ነው ሥራው?»

«ዛሬ ጠዋት አንዲት ሴር እንደሞቱ ያውቃሉ?»

«የለም፤ አላወቅሁም::»

«ለመታጠን የሚደረገውን ሁሉ ማድረግ አለብን:: ሟችዋ ሴር ቆመው ይጸልዩበት ከነበረው መሬት ስር አጽማቸው ያለሳጥን ማረፍ አለበት:: ነፍሳቸው ከሥጋቸው ከመለየቱ አስቀድሞ የጠየቁት ጥያቄ ነው:: መጠየቅ ሳይሆን ያዘዙት ነገር ስለሆነ መፈጸም ይኖርበታል::»

«ከዚያ ጸሎት ቤት ሰው መቅበር እኮ የተከለከለ መሆኑን ያውቁ የለ::»

«ወንዶች ናቸው የከለከሉት?፤ እግዚአብሔር ግን ይፈቅዳል::»

«ወሬ ቢሰማስ?»

«በእርስዎ ላይ እምነት አለኝ::»

«ግን አማሆይ፤ የጤና ጥበቃ ተወካይ...»

«የሃይማኖት መሪዎች ስለቀብር የደነገጉት ሕግ አለ::»

«ሆኖም የፖሊስ አዛዥ...»

«የጥንት ነገሥታት ፈትደዋል።»

«አስተዳዳሪው....»

«በእግዚአብሔር ፊት እርሱም ከቱጥር አይገባም።»

«አሁን እማሆይ?» አሉ ሽማግሌው።

«እምነት እንጣልብዎ?»

«እታዘዛለሁ።»

«በዚሁ ይለት።»

«እማሆይ ለጠቀሱት ሥራ ሁለት ሜትር የሚሆን ወፍራም ብረት ያስፈልገኛል።»

«የት ታገኛለህ?»

«አዚሁ ግቢ ውስጥ እቃ ከምናስቀምጥበት ሥፍራ ብረት ያሰ ይመስለኛል።»

«ይኸው ነው እማሆይ? አሁን ስላሉት በሰዓቱ እገኛለሁ።»

«የለም፣ ሌላም ነገር አለ።»

«ምን አለ?»

«የተገዛው የሬሣ ሣጥን ጉዳይ።»

ሁለቱም መልስ ሳይሰጡ ተፋጥጠው ለጥቂት ሰከንድ ቆዩ።

«የሬሣ ሣጥኑን ምን እናደርገዋለን?» ሲሉ ኃላፊዋ ጠየቁ።

«ይቀበራላ!»

«ባዶውን?»

«እማሆይ፤ እኔ ባፈር አሞላዋለሁ። አፈር ስሞላበት ሰው ያለው ይመስላል።»

«ልክ ነዎት። ሰውም ቢሆን እነ ከአፈር ነው የተሠራው። እንግዲህ ባዶውን ሣጥን እርስዎ ያዘጋጁታል?»

«በሚገባ!» ብለው ከመለሱ በኋላ ለመሄድ ወደ በር አመሩ።

«በመልዕክት አቀባበልዎ ደስ ነው ያለኝ። ወንድሙዎን ነገ ከእነ ዘንድ ያምጡት። ልጁንም ይዞ ይምጣ።»

ያን አለት ማታ ዣን ቫልዣ ከዚትን ይዞ ወደ ኃላፊዋ ሴር ሄዱ። ሴርዋ ዣን ቫልዣን ከእግር እስከ ራስ አዩት። ከዚትንም እንደዚሁ ከአየዋት በኋላ «ያህ ቤት ሳያስማማት አይቀርም» ሲሉ ተናገሩ።

ኃላፊዋ ሴር አብረዋቸው ከነበሩት ከለሎች ሁለት ሴሮች ጋር ጥቂት ተወያዩ። ከዚያም ኃላፊዋ ሚስተር ፎሽለማን እያዩ። «አቢታችን፣ ለላ ጉልበት ላይ የሚታሰር ቀጭል ይሰጥዎታል። አሁን እንግዲህ ሁለት ወንዶች ስለምትሆኑ ሁለት ቀጭል ነው የሚያስፈልጋችሁ» አሉ። በሚቀጥሉት ቀኖች የሁለት ቀጭል ድምፅ ከአትክልቱ ውስጥ ተሰማ። ሴሮች በዚያ ባለፉ ቁጥር ሁለት አትክልተኞች ዓን ሰዓን ሁነው እበባውን ሲኮተኩቱ ተመለከቱ። አንድ ቀን ጠዋት ሴሮች በብዛት በዚያ አለፉ። ሁለቱ አትክልተኞች ድምፅ ሳያሰሙ ይኮተኩታሉ። ወጥታው ድንጉት ደፈሰ።

«አብሮ የሚኮተኩተው ረዳት አትክልተኛ ነው» ካሉ በኋላ «የአባታችን ሚስተር ፎሽለማ ወንድም ነው» ሲሉ ተናገሩ።

ዣን ቫልዣ አዲሱ ስሙ ኧልቲመስ ፎሽለማ ሆነ።

ኃላፊዋ ሴት አንደተነበዩት ከዚት ግቢው ተስማምታት በአጭር ጊዜ ብዙ ጓደኛ አፈራች። አንድዋ ጓደኛዋ ኃላፊዋ ሴር ነበሩ። ከልጃገረዶች ትምህርት ቤት ውስጥ የነፃ ትምህርት እድል ተሰጥታት ትምህርትዋን ተጠለች።

❁❁❁

፪

ከዚት ገዳሙ ውስጥ ከሴቶች ትምህርት ቤት ገብታ ዩኒፎርም ስለሰች። ከእነ ሚስስ ቴናርዴዬ ቤት ስትወጣ የለበሰችውን ጥቁር ልብስ ዣን ቫልዣ ጥሩ አድርጎ ካጣጠፈው በኋላ ሳጥን ውስጥ አስቀመጠችው። ከዚያ ወዲህ እርስዋ አዳሪ ትምህርት ቤት ገዚታ ስትማር እርሱ የአትክልተኛነት ሥራውን ቀጠለ። ሥራውን በትጋት ስለሠራ ግቢው ውስጥ ለውጥ ታየ።

ከዚት በየቀኑ እየመጣች ለአንድ ሰዓት ያህል ከእርሱ ጋር ትጨዋወት ተፈቅዶላታል። ሴሮች ብዙውን ጊዜ ገሙ ስለሚልዎትና እርሱ ዘንድ በመጣች ቁጥር ብዙ ስለሚያጎሏት ዣን ቫልዣን ዘወትር ከሴሮች ጋር እያነፃፀረች እርሱን እንደ አምላክ ታመልከዋለች። ሁለቱ ወንዶች የሚኖሩበት ቤት እርስዋ ስትመጣ በጣም ይደምቃል። በአረፍት

ሰዓት ውጥተው ሲጫወቱ ጣጉ ቫልጣ ዘወትር በሩቁ ሆኖ ያያታል። ሳቅም የተለየ ስለነበር ድምፅዋን በሩቁ ይለየዋል። ከዚህም ያ ዝምታ ቀርቶ አሁን ሳቂታ ልጅ ሆናለች።

ከጊዜ በኋላ ከዚት በጣም እየተለወጠች ሄደች። ያ ኮሶ ፊትዋ በፈገግታ ተለወጠ። ሳቅ ብርሃን ስለሆነ ጨፍግጎት የነበረው ፊትዋ ብርሃን ፈነጠቀበት።

የእረፍቱ ሰዓት አልቆ ወደ ክፍልዋ ስትገባ ጣጉ ቫልጣ የክፍልዋን መስኮት በሩቁ ይመለከታል። ከዚያ ክፍል ውስጥ አንዴት ሁና እንደተቀመጠች ያሰላስላል።

ገዳሙ በአጋጣሚ ቢገባበትም ለእርሱ ሁለተኛው አስር ቤት ነበር። መጀመሪያ ታስሮበት የነበረው አስር ቤትና ገዳሙ በአንዳንድ ነገር ይመሳሰላሉ። ነገር ግን የመጀመሪያው እጅግ የመረረ ሲሆን የሁለተኛው እንደ መጀመሪያው የከፋ አልነበረም። ሆኖም ሁለቱም በስባድ አጥር የተከለሉና በራቸው በብረት መቀርቀሪያ የሚቀረቀር ነበር። አንዱ በወታደር አጥር ሲከበብ ሌላው በብርሃን መቅረዝ የተሞላ ነው። የመጀመሪያው ቅጣት የሚቀበሉበት ሥፍራ ሲሆን ሁለተኛው በጸሎት የሚማቅቁበትና ደግነት፣ ትህትናና ሩህሩህነት የሚታሰብበት ቦታ ነው። ከመጀመሪያው ይበልጥ ሁለተኛው ዝምታ ይበዛበታል።

ጣጉ ቫልጣ ሁለቱን በይበልጥ ባነፃጸረ ቁጥር ቅስሙ በይበልጥ እየተሰበረና የኑሮ ፍላጎቱም በይበልጥ እየደከመ ሄደ። ያለፈውን ሕይወቱን ወደኋላ እያየ ለራሱ ያዝናል። አንዳንዴ እስከ ማልቀስም ይደርሳል። በዚህ ዓይነት ከእስር ቤት ሲወጣ ያገኛቸው ጳጳስ በደግነታቸው፣ ከዚት በፍቅርዋና ገዳሙ በተገራ ኃይል የቀረጹበትን ውስጣዊ ስሜቱን እያመቀ ስድስት ወር ከገዳሙ ውስጥ ተቀመጠ።

የአትክልቱ ቦታ ፀጥታ፣ የአበቦች መዓዛ፣ የልጆች ጫጫታ የደናግሉ ዝማሬና ትህትና ቀስ በቀስ ሳይታወቀው ሕይወቱን ለወጡት። ልቡ በብቸኝነትና በዝምታ ኑሮ ስለተዋጠ ከመንፈሳዊ ኑሮ በስተቀር የሚያስበው ነገር ጠፍቶት እየኖረ ብዙ ዘመናት አለፉ። ከዚትም እያደገች ሄደች።



ማሪየስ

ምዕራፍ አሥራ ሦስት

ጋርሸለስ

ዣን ቫልዣና ክዜት ገዳም ከገቡ ከስምንት ወይም ከዘጠኝ ዓመት በኋላ አንድ ያልተጠበቀ ነገር ይሆናል። የአሥራ አንድ ወይም የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ የተቀዳደደ የትልቅ ሰው ጫማና ልብስ አድርጎ ቀና ጎዳና ላይ ይንቀዋለላል። ይህ ልጅ ልብሱን ያገኘው ከአባቱ ወይም ከእናቱ ላይሆን ለነፍሱ ብሎ ካደረ መንገደኛ ነው። እናትና አባቱ ግን በሕይወት አሉ። አባቱ ስለልጁ ደንታ የለውም፤ እናቱም ብትሆን እስከዚህም አትወደውም። ይህ ልጅ እናትና አባት እያላቸው ቤተሰቦቻቸው የትም እንደሚጥልዋቸው እንደማናቸውም ልጆች የሚታዘንለት ልጅ ነበር።

ልጁ መንገድ ለመንገድ በሚዞርበት ጊዜ በጣም ደስ ይለዋል። መንገድ ላይ የተነጠፈው ድንጋይ እንደ እናቱ ልብ ደንድኖና ጠጥር አይቆረቁረውም። እናትና አባቱ ክዜት አስወጥተው የትም ጥለውታል።

ልጁ በጣም ጉቱ፤ ቀልጣፋና ሥላ ልጅ ቢሆንም ታሞ የዳነ ይመስል ሰውነቱ ከመገርጣት አልፎ ክስት ብሏል። ይሮጣል፤ ይዘላል፤ ይጫወታል፤ ይዘፍናል፤ የማያደርገው ነገር የለም። ሲያመቸው ይሠርቃል፤ ሳያመቸው ይለምናል። አለዚያም ይቆምራል። ከጮሌነቱ ብዛት «ልጅ» እያሉ ሲጠሩት ከመቅጽበት ከተፍ ይላል። የሚለብሰው ልብስ፤ የሚበላው ምግብና የሚጠለልበት ማደሪያ ወይም ደግሞ የሚወደውና የማያፈቅረው ሰው የለውም። ነገር ግን ነፃ ሆኖ በመኖሩ ደስተኛ ነው።

ከእንደነዚህ ያሉ ሰዎች ላይ ጎብረተሰብ ይጨክናል። ከጭካኔው ብዛት አድቅቆ ይፈጫቸዋል። ግን ልጆች ከዚህ ዓይነቱ ጭካኔ አልፎ አልፎ ያመልጣሉ። ትንንሽ ልጆች በመሆናቸው በመጠኑም ቢሆን ህብረተሰብ ስለሚያዝንላቸው ያልፋቸዋል። ልጆቹም ማምለጫ ቀዳዳ አያጡም።

ሆነም ቀረም፤ ይህ ብቸኛ ልጅ በየሁለት ወይም ሦስት ወር «አሁንስ እናቴ ጋ እሄዳለሁ» እያለ በየጊዜው ለራሱ ቃል ይገባል። ወደዚያው ለመሄድ መንገድ ጀምሮ ከተወሰነ ሥፍራ ሲደርስ «አሁንስ ወጄት ነው የምሄደው?» በማለት ራሱን በመጠየቅ ይቆማል። ቆም ብሎ ራሱን የጠየቀው ከአሁን ቀደም ከጠቀስነው ቁጥሩ 50-52 ከሆነ ቤት በራሩ ነበር።

በተጠቀሰው ጊዜ ቤቱ ላይ «የሚከራዩ ክፍሎች» የሚል ጽሑፍ ከበሩ ላይ ተንጠልጥሎአል። ዣን ቫልዣ ከዚያ ሥፍራ ክፍል በተከራየበት ጊዜ የነበረችው የቤቱ ጠባቂ ሞታለች። ልክ እርስዎን የምትመስል ሌት

ተዕለት ትሠራለች። ስምዋ ማዳም ቡርዣ ይባላል።

ከዚያ ቤት ውስጥ ክፍል ከተከራዩት ሰዎች መካከል አንዱ አራት በተሰበ ያለው መናጢ ድሃ ይገኝበታል። እነዚህ እናት፣ አባትና ለአትመ- ልጆን የደረሱ ሁለት ሴቶች ልጆች የሚኖሩት ከአንድ ክፍል ውስጥ ነው። የመንደር ለመንገድ የሚንከራተተውም ልጅ የዚህ ቤተሰብ ልጅ ነበር። ልጁ ከዚያ ቤት ሲደርስ የቆመው ልግባ ወይስ አልግባ በሚል የሕሊና መንታ መንገድ ነበር።

ቢገባ ያው ኩርፊያና ዱላ ነው የሚጠብቀው። የመጀመሪያው ጥያቄ ሪነም «ከየት መጣህ?» የሚል ይሆናል። መልሱም «ከበረንዳ» ይሆናል። ተመልሶ ሊወጣ ደግሞ «የት ነው የምትሄደው?» ብለው ይጠይቁታል። መልሱም «ወደ በረንዳ» ነው የሚሆነው። እናቱ ይህን ጊዜ «ታዲያ አሁን ምን መጣህ?» ብላ ትጠይቀዋለች።

እውነተኛ የአባት ወይም የእናት ፍቅር ለምን እንደሆነ ስለማያውቅ ልጅ በዚህ ቅር አይሰኝም። እናቱ የልጁን አህቶች በጣም ትወዳቸዋለች። አደ የሚጠራው በእውነተኛው አባቱ ስም ሳይሆን በሌላ ነው። ምነው ጊዜ፣ የዚህ ዓይነት የተበላሸና የተመሰቃቀለ ኑሮ የሚኖሩ ሰዎች ዘራቸውን መቋረር አይፈልጉምና ነው።

እነዚህ ቤተሰቦች የሚኖሩበት ክፍል የሚገኘው ከአንድ ጥግ ሲሆን ዘለ አቅጣጫ ከጥግ ያለውን ክፍል የተከራየው ሰው ደግሞ ማሪየስ ሚባል ወጣት ነበር።

ይህ ማሪየስ የተባለው ወጣት ማነው?

የታመቀ ቡርዣዋ

ፓሪስ ከተማ ውስጥ ለብዙ ዓመታት ከኖሩ ሰዎች መካከል አንዱ ሚሊ ጊልኖርማንድ የሚባሉ አንድ ሽማግሌ ነበሩ። በ1831 ዓ.ም «ለረጅም ከመን ኖረዋል» ተብለው ከሚጠቀሱት ሰዎች መካከል አንዱ እኚህ ሰው ነው። ሰውዬው እድሜያቸው በጣም በመግፋቱ «ትውልድ የተላለፈበት» ሚል የቅጽል ስም ይታወቃሉ። እኚህ ሰው በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኖሩ የእውነተኛ ቡርዣዎች ርዝራዥ በመሆናቸው ብዙ ሀብት አላቸው። ሂሚያቸው ወደ ዘጠና ዓመት ይሆናል። ብዙ ጊዜ ቆሎ የመቆጣት ሚት ይጠናወታቸዋል። ሲናገሩ ይፎሃሉ። በዚህ እድሜያቸው ብዙ ኒሳሉ፤ ይጠጣሉ፤ ቀጥ ብለው ይራመዳሉ። ከስላሳ ሁለት ጥርሶቻቸው ሚከል አንዱ እንኳን አልወለቀም። ዓይኖቻቸው አልደከሙም፤ ሲያነቡ

ብቻ ነው መነጽር የሚያደርጉት። ዝቢያቸው ከፍተኛ ቢሆንም ድሃ እንጂ ሀብታም ነኝ አይሉም። አሽከሮቻቸውን መደብደብና ማንቋሸሽ ይወዳሉ። ሃምሳ ዓመት ያለፋት ያላገባች ሴት ልጅ አለቻቸው። ሲከፋቸው ሴትዮዋን ከመቆጣት አልፈው ይገርፏታል። በእርሳቸው ዓይን ልጅቱ የሃምሳ ሳይሆን የስምንት ዓመት ልጅ ናት።

ሰውዬው የሚኖሩት በራሳቸው ቤት ሲሆን ቤታቸው ባለ ብዙ ፎቅ ነው። ግቢው እጅግ በጣም ሰፊ ሲሆን በአሽበረቱ አበቦችና ዛፎች ተሸፍኖአል። ሸማግሌው በወጣትነት ዘመናቸው ብዙ ሴቶች አታልለዋቸዋል። ሆኖም አሁንም ቢሆን በዘጠና ዓመታቸው ራሳቸውን ወጣት አድርገው ነው የሚገምቱት። አለባበሳቸውም እንደወጣት ነው። ነገር ግን በወጣቶች የሚመራውን የፈረንሳይ አብዮትን እጅግ በጣም ይነቅፋሉ። እርሳቸው እየሰሙ አንድ ሰው የነገሥታትን አገዛዝ ነቅፎ ሪፐብሊክ የሚመሠረትበትን ሁኔታ ቢናገር ፊታቸው ከመቅጽበት ደም ይለብሳል። ይህን ሲሰሙ በጣም ስለሚቆጡ ራሳቸውን እስከ መሳት የሚደርሱበት ጊዜ ነበር።

የወንድና የሴት አሽከሮች በብዛት አሉዋቸው። ሠራተኞቹን በጎሣቸው እንጂ በራሳቸው ስም አይጠሯቸውም። ለምሳሌ አንድ ቀን አዲስ የወጥ ቤት ሠራተኛ ለመቅጠር ፈልገው ሰዎችን ያነጋግራሉ።

«ደመወዝ ስንት ትጠይቂአለሽ?»

«ሰላሣ ፍራንክ»

«ስምሽ ማነው?»

«አሉምፒ»

«ሃምሣ ፍራንክ እንክፍልሻለን፤ ስምሽ ግን ኒክሌት ይሆናል።» (ኒክሌት የአንድ ጎሣ ስም መሆኑ ነው።)

ሁለት ሚስቶች ነበሩዋቸው። ከሁለቱም አንዳንድ ሴት ልጅ ሲወለዱ አንደኛዋ ልጅ በሰላሣ ዓመትዋ ነው የሞተችው። ባል አግብታ ነበር። ባልዋን ያገባችው አፍቅራና ተፈቅራ ወይም በአጋጣሚ ይሁን አይታወቅም። ወታደር ነበር። በትልቅ እህትዋና በእርስዋ መካከል የአሥር ዐመት የዕድሜ ልዩነት ነበር። ትንሽዋ ስታገባ ትልቅዋ ቆማ ትቀራለች። ምናልባት በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም፤ ትልቅዋ ልጅ ዘወትር ትተከዛለች። የምትተክዝበትን ትክክለኛ ምክንያት ግን ከራስዋ በስተቀር የሚያውቀው የለም። ሕይወትዋ በድን ለመሆኑ ፊትዋ ይመሰክራል።

ከአባትዋ ጋር ነው የምትኖረው። በታሪኩ መጀመሪያ ያየናቸው ጳጳስ ከአህታቸው ጋር እንደኖሩ ሁሉ እኚህ ከበርቴ ደግሞ ከልጃቸው ጋር

ነው የሚኖሩት። አንደኛው የሌላው ደጋፊ ነው።

ከቤቱ ውስጥ ከአባትና ልጅ ሌላ አንድ ልጅ ነበር። ይህ ልጅ ተሸዋቂውና ተንቀጥቅጦ ነው ያደገው። ሚስተር ጊልኖርማንድ ልጁን ፈጥጣ እንጂ በለዘበ አንደበት አናግረውት አያውቁም።

«ና በል! ወሮበላ፤ ጥፋ፤ ሰማህ፤ ዱርዬ፤ መልስ እንጂ፤ አህያ...» ልጁ ዘወትር የሚሰማቸው ቃሎች ናቸው። ሚስተር ጊልኖርማንድ ልጁን በእንደነዚህ ዓይነት ስሞች በቁጣ ሲጠሩት በእጃቸው ለበቅ ይዘው ነው። ልጁ ግን ሰውዬውን እንደ አምላክ ነው የሚያያቸው። ልጁ የሸማግሌው የልጅ ልጅ ሲሆን ስለልጁ ወደፊት ብዙ እንሰማለን።

❄❄❄

ምዕራፍ ስሥራ አራት

አያትና የልጅ ልጅ

ቪርኖን ከተባለች ትንሽ ከተማ ያለፈ ሁሉ አንድ ወደ ሃምሣ ዓመት እድሜ ያለው ከአድሚው በላይ ያረጀ፤ የተጨማደደ ቆብ ያጠለቀ፤ የተጫጨቀ ልብስ የለበሰ፤ ፊቱ በፀሐይ ብዛት የጠቆረ፤ ፀጉሩ የሸበተ፤ ፊቱ ላይ ትልቅ ጠባሳ ያለበት፤ ወገቡ የጎበጠ፤ ዘወትር አካፋና የአትክልት መኮርኮሚያ ይዞ የሚራመድ፤ ከሴን ወንዝ ድልድይ አካባቢ የማይጠፋ ሰው ሳያይ አያልፍም። የተጠቀሰው ሰው በ1817 ዓ.ም. እጅግ በጣም አስቸኖኛ ከሆነ ቤት ውስጥ ይኖር ነበር። ይህ ሰው በድኅነት አየማቀቀ አንዲት አሮጊት አይልዋት ልጅ፤ ቆንጆ አይልዋት ፋንታ፤ ከበርቴ አይልዋት ደግ፤ ከተማ አይልዋት ገጠሬ ሴት ጋር ይኖራል። ሰውዬው ጠዋት ማታ ከሚጋክከበው የአበባ ሥፍራ ተለይቶ አያውቅም። ኑሮውን የሚገፋው አበባ አየሸጠ ነው።

ይህ ሰው በአፍላው ዘመን ጦር ሜዳ ትልቅ ጀብዱ የፈጸመ ሲሆን ከጄኔራል ፓንትመርሲ ይባላል። በልጅነቱ በወታደርነት ተቀጥሮ ዋተርሉ ከሚባለው ጦር ሜዳ ሠራዊት እየመራ ዘምቷል። ጦር ሜዳ ላይ የጠላት ጦር መሣሪያ ማርኮና በደም ተበክሎ ከንጉሡ ፊት በቀረበ ጊዜ «አይ ቪኛ፤ የጀግና ዛር» ተብሎ ከተሞገሰ በኋላ የኮሎኔልነት ማዕረግና የጀግና ሽልማት ይፈቀድለታል። ማዕረጉና ሽልማቱ እንደተፈቀደለት

«ግርማዊ ሆይ! በባል አልባ ባለቤቱ ስም አመሰግናለሁ» ብሎ ይናገራል። ይህንን ከተናገረ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሕሊናውን ስቶ ከመሬት ይዘረራል። ይህ ጀግና ወታደር ነው ዛሬ የአበባ ሻጭ ሆኖ በችግር የሚማቅቀው።

ጀርጅ ፓንትመርሊ በጦርነቱ ስለተጎዳ እጅግ አነስተኛ የሆነ የጡረታ አበል ተፈቅዶለት ቬርናን ከተማ እንዲመለስ ተደረገ። የሚያሳዝነው ንጉሡ ቃላቸውን ረስተው ለሰውዬው ምንም እንኳን ሸ·መቱና ሚዳሊያው ቢሰጠውም እነዚህ ነገሮች ያስገኙት የነበረውን ጥቅም ሳያገኝ ቀረ። ሆኖም ከቤቱ በወጣ ቁጥር የጀግንነት ሜዳልያውን ሳያደርግ አይወጣም።

የጡረታው ገንዘብ በጣም ትንሽ ስለነበር በጣም ዝቅተኛ የሆነ ቤት ተከራየ። በዚህ ጊዜ ነበር የከበርቴው መሴይ ጊልናርማንድን ልጅ ያገባው። የከበርቴው ልጅ ይህን ድሃ በማፍቀርዋ አባትዋ ከማዘን አልፈው በጣም ይናደዳሉ። ነገር ግን እርስዋ ከፈለገች መቼስ ምን ይደረጋል በሚል ቢጋብቻው ተስማሙ። የሚያሳዝነው ግን ሴትዮዋ ምንም እንኳን እጅግ ተናፋቂና ተወዳጅ ሴት ብትሆንም ብዙ አልኖረችም። በ1815 ዓ.ም ሕፃን ልጅ ከኋላዋ ትታ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች። ልጁ የኮለ·ኔሉን የብቸኝነት ኑሮ ለመለወጥ የደስታ ምንጭ መሆን ይገባው ነበር። ግን ሊሆን አልቻለም፣ ምክንያቱም አያቱ «ልጁ ለእኔ ካልተሰጠኝ ሀብቱን አላወርሰውም» ስላሉ ልጁ ከአባቱ ተነጠለ። አባት ጥያቄውን የተቀበለው ለልጁ ሲል ነበር። የወለደውን ልጅ ለማግኘት ባለመቻሉ የልጁን ፍቅር በአበባ ፍቅር ለወጠው።

መሴይ ጊልናርማንድ ከሴት ልጃቸው ባለቤት ጋር የቀረበ ግንኙነት አልነበራቸውም። ለአርሳቸው ኮለ·ኔሉ «ሽፍታ» ነው። ኮለ·ኔሉም ሽማግሌውን ነገር እንደማይገባቸው «ደደብ» ሰው ነበር የሚያያቸው። መሴይ ጊልናርማንድ ሁኔቱ ካላስገደዳቸው ወይም ለመፎተት ካልሆነ በስተቀር ስለኮለ·ኔሉ ማንሳት አይፈልጉም። አባት «ልጄን ካላየሁ ወይም ካላነጋገርኩ» እያለ ቢያስቸግር ልጁ የአያቱን ሀብት ሊወርስ እንደማይችል ለኮለ·ኔሉ በቅድሚያ ተገልጾለታል። ኮለ·ኔሉ በዚህ መስማማቱ ምናልባት ጥፋተኛ ሳይሆን አልቀረም። ግን ይህን ግዳጅ የተቀበለው ለልጁ በማሰብና የራሱን ደስታ በመሰዋት ሲሆን የወለደው እርምጃ ትክክል መሆኑን ስላመነ ነው።

ልጁ በቀጥታ ከአያቱ ሊወርሰው የሚችለው ሀብት እስከዚህም ብዙ አልነበረም። ከእናቱ ታላት እህት ማለት ከአክስቱ ሊወርሰው የሚችለው ሀብት ግን እጅግ ብዙ ነበር። አክስቱ በእናትዋ በኩል የወረሰችው ብዙ ሀብት ነበራት። የእህትዋ ልጅ ደግሞ ቀጥተኛ ወራሽ ነው። የልጁ ስም ማሪየስ ይባላል። ማሪየስ አባት እንዳለው ያውቃል። ከዚያ ወዲያ ስለአባቱ የሚያውቀው ነገር የለም። አንዲያውም ከነአካቴው በአካባቢው የሚወራውን ሐሬ ስለሰማ በአባቱ ያፍራል።

የማሪየስ አባት በዋተርሉ ጦርነት ሦስት ጠር ፓሪስ ከተማ እየመጣ ልጁ አያቱ ጋር ወደ ቤተሰቦቹ ሲሄድ ያየዋል። የምለውን ቃል አናርሶ እነሆን የሚያየው ሰው እንዲያነሳው ተጠንቅቆ ከአሳቻ ሥፍራ በመደበቅ ነበር ልጁን የሚያየው።

ማሪየስ እንደማንኛውም ልጅ ትምህርት ቤት ገብቶ ይማራል። የታውቀ ዝነኛ አስተማሪ ከቤት ተቀጥሮለት ትምህርቱን በማገባ ይከታተላል። ኮሌጅ እንደገባ በኋላ የሕግ ትምህርት ለመከታተል ከሕግ ትምህርት ቤት ገባ። ለአያቱ ብዙም ፍቅር የለውም። የአያቱ አሻሙርና ንቀት ልቡን አቁስሎታል። የወላጅ አባቱ ጉዳይ ግን ዘወትር ያሳስበዋል። ልጁ ቡተፈጥሮው ጨዋ፣ ረጋ ያለ፣ በራሱ የሚተማመን ኩሩ ልጅ ነበር። ከዚህም በላይ ፈረሃ እግዚአብሔር ያደረበት ነው። በ1827 ዓ.ም ማሪየስ የአሥራ ስምንት ዓመት ወጣት ነው። አንድ ቀን ማታ አያቱ ከነበሩበት ክፍል ሲገባ ደብዳቤ በእጃቸው ይዘው ደረሰ።

«ማሪየስ» አሉ መሴይ ጊልናርማንድ፣ «ነገ ጠዋት ወደ ቬርናን ትሄዳለህ።»

«ለምን?» ሲል ማሪየስ ጠየቀ።

«አባትህን ለማየት።»

ማሪየስ ደነገጠ። አንድ ቀን ከአባቱ ጋር አንናኛለሁ የሚል አሳብ በሕውኑም ሆነ በሕልሙ አስቦት አያውቅም። ምንም ነገር ከዚህ ያለፈ ጥፋተኛና ያልተጠበቀ ሊሆንበት አይችልም ነበር።

በሀገሪቱ ውስጥ ስለነበረው የፖለቲካ አቋም የተቀውሞ አሳብ ቢኖረውም አያቱ እንደሚሉት አባቱ የቡርቮዎን አገዛዝ የሚቀውም «የማይረባ ወታደር» ነው። በዚህ የተነሣ ለአባቱ የነበረው ፍቅር ይህን ሰህል አልነበረም። ከዚህም በላይ ወላጅ አባቱ እርሱን ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠቱ ጭካኔ ስለመሰለው ጠላው። «አባቱ አይወዳኝም» ሲል አመነ። ይህ በዚህ እንዳለ በዚያች ቅጽበት ያልጠበቀው ጥያቄ ከአያቱ ስለመጣ በመደንገጡ የአያንታም ሆነ የአምቢታ መልስ ለመስጠት አልቻለም። አያቱ ንግግራቸውን ቀጠሉ።

«አባትህ ታሚል መሰለኝ፣ ሊያይህ ይፈልጋል።»

በሚቀጥለው ቀን ጀምበር ልትጠልቅ ስትል ማሪየስ ከቬርናን ከተማ ሲደ. በመጀመሪያ ያገኘውን ሰው «የመሴይ ፓንት መርሊ ቤተ የት እንደሆነ ያውቃለ?» ሲል ይጠይቃል።

ተጠያቂው ቤቱን ያውቅ ኖሮ አመላክተው። ከዚቱ ሲደርስ በሩን በመደብደብ እንኳኳ። እንዲት ሴት በሩን ከፈተችለት።

«መሴይ ፓንትመርሲ አለ?» ሲል ማሪየስ ጠየቀ።

ሴትዮዋ ደንግጣ መልስ ሳትሰጠው ገዘም ብላ ቆመች።

«አሉ እንዴ?» ሲል እንደገና ጠየቀ።

ለመኖሩ ግምባርዋን ወደ ላይ በመግፋት አረጋገጠችለት።

«ላነጋግራቸው እችላለሁ?»

እንደማይቻል ጭንቅላትዋን በመነቅነቅ ገለጸችለት።

«እኔኮ ልጃቸው ነኝ» አለ ማሪየስ። «እንደምመጣ ደግሞ ስለሚያውቁ ይጠብቁኛል።»

«ከእንግዲህ ወዲያ አይጠብቅህም» አለች ሴትዮዋ።

በዚህ ጊዜ አተኩሮ ሲመለከታት ቀይም ሲል ታለቅስ እንደነበር አወቀ።

ወደ አንድ ክፍል ባመለከተችው ጊዜ ወደ ክፍሉ ገባ። ክፍሉ ውስጥ ሦስት ሰዎች ነበሩ። አንዱ ቆሞአል፤ ሌላው ተንበርክኮአል። ሦስተኛው ከመሬት ላይ ተንጋልሎ ተኝቷል። ተጋልሎ የተኛው አባቱ ነው። ከሁለቱ ሰዎች አንደኛው ሐኪም ሲሆን ሌላው ጸሎት የሚያደርሱ ቄስ ነበሩ።

ኮሎኔሉ በጠና ከታመመ ሦስት ቀን ሆኖታል። ወዲያው ሕመሙ እንደጀመረው ነበር ልጁ አንዲመጣለት በመልክተኛ ደብዳቤ ለመሴይ ጊልናርማንድ የላከው። ደብዳቤውን እንደላከ ሕመሙ እየጠናበት ሄደ። ማሪየስ ቬርናን በደረሰበት አለት ልጁ ከመድረሱ በፊት «ልጄ አልመጣም? እሱ ካልመጣ እኔ ሄጀ እገናኘዋለሁ» እያለ ካልጋው ዘሎ ይወርዳል። ሠራተኞች ሊይዙት ቢሞክሩም ሊይዙት ባለመቻላቸው ከክፍሉ ወጥቶ ከበረዳ ሲደርስ ይወድቃል። እዚያው እንደወደቀ ሕይወቱ አለፈች።

ሕይወቱ ከማለፉ በፊት ሐኪም እንዲመጣ ሰዎች ተሯሯጡ። ነገር ግን ሐኪሙ ከመድረሳቸው በፊት ኮሎኔሉ ሞተ። ቄሱም ቢሆኑ ነፍሱ ከወጣ በኋላ እንጂ አስቀድመው አልደረሱም። ልጁ ግን የደረሰው ዘግይቶ ነው።

ክፍሉ ውስጥ የነበረው መብራት ደብዛዛ ቢሆንም ከኮሎኔሉ ጉንጭ ላይ ከመሞቱ በፊት አምባ መውረዱ ያስታውቃል። እንዲያውም አምባው ጨርሶ አልደረቀም። ያለቀሰው ልጁ በጊዜው ስላልደረሰለት ነበር።

ማሪየስ ሰውዬውን አፍጥጦ ተመለከተው። ለመጀመሪያና ለመጨረሻ ጊዜ ነበር አባቱን ያየው። የአባቱ ዓይኖች ቢገለጡም እርሱ ያያቸዋል እንጂ አነርሱ አያዩትም። የአባቱ እጅ ተገልጦ ስለነበረ የጦር ሜዳ ቁስሎቹ ጠባሳ በብዛት ይታያሉ። ከፊቱም ላይ ትልቅ ጠባሳ አለ። አባቱ እንደሆነና ሕይወቱ እንዳለፈች ማሪየስ አወቀ። በድንጋጤ ክው ስላለ ከአልጋው አልተነቃነቀም። ያዘነው ሀዘን ወደር አልነበረውም። እንኳን የወለደው አባቱ ማንም ሰው ቢሆን እንደዚያ ተዘርሮና ሞቶ ቢያይ በጣም ማዘኑ አይቀርም።

ሀዘን፤ መሪር ሀዘን ከዚያች ክፍል ውስጥ ሰፍኖአል። ሠራተኛዋ ሁሉ ቆማ ታነባዋለች። ቄሱ ይጸልያሉ፤ ግን እየጸለዩ ሲንሰቀሰቁ ይሰማል። ሐኪሙ ወዲያው፤ ወዲያው ዓይናቸውን በመሐረብ ይጠርጋሉ። ሬሳውም ቢሆን የሚያለቅስ ይመስላል።

ሐኪሙ፤ ቄሱ፤ ሴትዬዋ ቃል ሳይተነፍሱ ማሪየስን አዩት። ከውጭ የመጣ እንግዳ እሱ ብቻ ነው። ማሪየስ ከነበረበት ትንሽ ነቅነቅ አለ። በጣም እፍረት ተሰማው። ያደረገውን ቆብ አውልቆ በእጅ ይዞት ስለነበር ላይታወቀው ከእጁ አምልጦ ከመሬት ወደቀ። ነገር ግን በጣም ከማዘኑ የተነሣ ቆቡን እንኳን ለመያዝ አትም እንደሌለው ለማሳየት እንጂ እውነትስ አምልጦት አልነበረም።

ስለአባቱ የነበረውን አመለካከትና ግምት አስታውሶ ተጸጸተ። መጸጸት ብቻ ሳይሆን ራሱን በጣም ነቀፈ። ግን ጥፋቱ የእርሱ ነው?

ኮሎኔሉ ወደኋላ የተወው ሀብት አልነበረም። ከቤቱ ውስጥ የነበሩት እቃዎች ተሽጠው ለተብሩ የወጣውን ወጪ እንኳን ለመሸፈን አልቻሉም። ሠራተኛዋ አንዲት ወረቀት አግኝታ ለማሪየስ ሰጠችው። ኮሎኔሉ ከመሞቱ በፊት የጻፈው ማስታወሻ ሲሆን ቃሉም የሚከተለው ነው።

«ለምወድህ ልጄ፤ ዋተርሉ ጦር ሜዳ ላይ በተደረገው ጦርነት ስፈጸምኩት ጀብዱ የባሮንነት ማዕረግ ተሰጥቶኝ ነበር። ማዕረጉን ቢደሜ የምጀሁት ስለሆነ ለልጄ ማውረስ እችላለሁ። እኔ አሁን ማዕረጉ ይጮነቃል ወይም አይገባውም ብዬ መናገር የለብኝም።» ከወረቀቱ ጀርባ ላይ ኮሎኔሉ የጻፈው ማስታወሻ ደግሞ «በዚሁ በዋተርሉ ጦርነት አንድ የሃምሣ አለቃ ሕይወቴን አድኖአል። ስሙ ቴናርዲዬ ይባላል። ከፓሪስ ኩተማ ወጣ ብሎ ምንትፌርሜ ከተባለ ሥፍራ አንዲት አነስተኛ ሆቴል እንደነበረው አውቃለሁ። ድንገት ካገኘኸው በተቻለህ አርሱን እርዳልኝ» የሚል ነበር።

የአባቱ ፍትኮር አስገድዶት ሳይሆን «የሞተን አክብር» ብሎ በሚገፋፋን ውስጣዊ ኃይል ተመስጦ ማሪየስ ወረቀቱን በኃይል ጨመደደው።

ስለኮሎኔሉ ከዚያ በኋላ የታወቀ ነገር የለም። ዩኒፎርሙንና ጉራዴውን መሴይ ጊልናርማንድ ለውራጅ እቃ ሸማች ሸጡት። ኮሎኔሉ የተከላቸውን አበቦች ጎረቤቱ ቀጥፈውና አትክልቱን አበላሽተው በአጭር ጊዜ ውስጥ ድራሹን አጠፉት።

ማሪየስ ለሁለት ቀን እዚያው ቬርኖን ቆይቶ ከቀብሩ ሥነሥርዓት በኋላ ወደ ፓሪስ ተመለሰ። ከዚያም የአባቱ መሞት ብዙም ሳይረብሸው ትምህርቱን ቀጠለ። ኮሎኔሉ በሞተ በሁለተኛው ቀን ተቀበረ፤ በሦስተኛ ቀን ተረሳ።

❀❀❀

፱

ማሪየስ ለጥቂት ቀናት ከኮቱ ኮሌታ ላይ ጥቁር ጨርቅ አደረገ። የሀዘን ምልክት መሆኑ ነው። ከዚህ ሌላ የተደረገ ነገር አልነበረም።

ማሪየስ ካደገ በኋላም እንደ ልጅነቱ ቤተክርስቲያን መሄዱን አላቋረጠም። በልጅነቱ ከአክስቱና ከአያቱ ጋር ዘወትር ነበር የሚሄዱት። የሚሄዱት ደግሞ ቀደም ሲል ከተነጋገርንበት ከደግናል ጸሎት ቤት ነበር።

አንድ ቀን እሑድ እንደለመደው ቤተክርስቲያን ሄዶ ከጀርባው «መሴይ ማብዩፍ ቸርች ምርደን» ተብሎ ከተጻፈበትና በወይን ጠጅ ቀለም ከተለበደ ወንበር ላይ ይቀመጣል። ጥቂት እንደቆየ አንድ ሽማግሌ ይመጡና «ወንድም ይቅርታ፤ ይህ ቦታ ለእኔ የተመደበ ነው» ይሉታል። ማሪየስ በአሳብ ጭልጥ ብሎ ሄዶ ነበር። ከአሳቡ ሲነቃ ማሪየስ ወንበሩን ለሽማግሌው ይለቅላቸውና ሽማግሌው ይቀመጣሉ።

ቅዳሴ ካለቀ በኋላ እንኳን ማሪየስ ከሐሳቡ አልወጣም። ለሽማግሌው ወንበሩን ይልቀቅላቸው እንጂ ከሥፍራው ርቆ አልሄደም። ሽማግሌው የማሪየስ ከሐሳብ ባህር መዘፈቅ አይተው ከቅዳሴ በኋላ አናገሩት።

«ይቅርታህን ልጄ! ቅድም አስቀየምኩህ መሰለኝ። ምናልባት 'ምን ዓይነት ደፋር ሰው ነው' ብለህ ታዝበኸኝ እንደሆነ ላስረዳህ።»

«ጌታዬ» አለ ማሪየስ፤ «ምንም አያስፈልግም።»

«የለም» ሲሉ ሽማግሌው ቀጠሉ፤ «ተቀይመኸኝ እንድትሄድ አልፈልግም። ስለዚያች ቦታ ብዙ የማስታውሰው ነገር አለኝ። ለዚህች ቦታ የተለየ ስሜት አለኝ። እንደዚያ ያልኩትም ያለ ምክንያት አይደለም። ታሪኩን ላጫውትህ።»

«አንድ ብርቱ ሰው ነበረ። ይህ ሰው እጅግ በጣም የሚወደው ልጅ አለው። ሰውዬው በአንድ ውርስ ምክንያት ከልጁ ጋር ይለያያል። ኑሮለያየም ልጁን ተመልሶ አንዳያይ ይደረጋል። አባት ልጁን ይወድ ስለነበር ሠላሳት ወይም ሦስት ወር ከዚህች ሥፍራ እየመጣ ካስነሳህህ ቦታ አለመጣ ካለው ምስሶ ተደብቆ ልጁን አይቶ ይሄዳል። አሥር ዓመት ሙሉ ለላ ሥራ ሳይኖረው ከዚህ እየመጣ ልጁን አይቶና አንባውን አፍስሶ ይሄዳል። ልጁ አባቱን ስለማያውቅ የሰውዬው መመላለስ ልብም አይልም። ከሰውዬው ጋር ከጊዜ በኋላ ተዋወቀን ነው ታሪኩን ያጫወተኝ። ሰውዬው አንድ ሀብታም አማች ነበረው። አባት ልጁን መጥቶ ቢያይ የአያቱንና የአክስቱን ብዙ ሀብት ሊወርስ አይችልም ብሎ ማን እንዳስፈራራው ትገለጽም። ብቻ አባት ልጁ አንድ ቀን ያንን ሀብት ወርሶ ደስ ብሎት ይኖራል በሚል እምነት የራሱን ደስታና ፍቅር መስዋዕት አደረገ። የልጁ አባትና አያት ደግሞ በዘመኑ ባለው የፖለቲካ ሽኩቻ የተነሣ እንደማይስማሙም አጫውተውኛል። ስለፖለቲካ ጉዳይ መወያየቱ መልካም ነው። ግን አንዳንድ ሰዎች የፖለቲካ ወሬ ከጀመሩ ማባሪያ የላቸውም። ከዚህም በላይ የአንዱን ወገን ይዘው ጭልጥ ብለው ወደ አንድ አቅጣጫ ይሄዳል። ለምሳሌ አንድ ሰው አንዱን ወገን ተከትሎ ዋተርሉ ላይ ስለተዋጋ ቸ መኖሮ ሰው ነው ለማለት ያዳግታል። አባትንና ልጅን በዚህ የተነሣ ግለያየት ደግሞ ተገቢ አይሆንም። አሁን የምልህ ሰው ከቦናፓርቴ ጦር ውስጥ ኩሎኔል ነበር። ዛሬ እንኳን ሰውዬው የሞተ ይመስለኛል፤ ቬርኖን ከተባለ ከተማ ይኖር ነበር። ወንድሜ ቂስ ሲሆን የሚኖረው ከዚያ ከተማ ውስጥ ነው። የሰውዬው ስም ፓንትመርሲ ይባላል።»

ልጁ «ፓንትመርሲ!» ብሎ ስሙን ደግሞ ከተናገረ በኋላ ፊቱ ሰይል ይለዋወጣል።

«አዎን ፓንትመርሲ፤ ታውቀዋለህ?»

«አባቴን» አለ ማሪየስ፤ «የሚሉት ሰው አባቴ ነበር።»

ሽማግሌው እጁን በእጁ መታ። «ያ ልጅ ማለት አንተ ነህ! ልክ ነው፤ ልጁ የአንተን እድሜ ሊይዝ ይችላል። እንግዲያውስ ልጁን በጣም የሚወድ አባት ነበረኝ ብለህ ልትኩራራ ይገባሃል።»

ሽማግሌውና ማሪየስ ብዙ ተጫወቱ። በመጨረሻ እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደ ሽማግሌው ቤት ሄዱ። በሚቀጥለው ቀን ማሪየስ አያቱን ሊያቁ ጠየቃቸው።

«ከጥቂት ጓደኞቼ ጋር አደን ለመሄድ ተነጋግረን ነበር። ለሦስት ቀን ከእነርሱ ጋር ብሄድ ትፈቅድልኛለህ?»

«ለአራት ቀንም መሄድ ትችላለህ። ሂድና ራስህን አስደስት» አሉት። ሽማግሌው ወደ ሴት ልጃቸው ዞር ብለው ከጠቀስዋት በኋላ «የኒትር ጉዳይ ይሆናል!» አሉዋት በሹክሹክታ። ሽማግሌው ያሰቡት ዓይነት ፍትር ላይሆን የአባት ፍቅር ነበር።

ማሪየስ ወደ ቬርኖን ሄዶ ከአባቱ መቃብር አጠገብ ብዙ ጊዜ አጠፋ። ከቬርኖን ሲመለስ በቀጥታ ወደ ሕግ ትምህርት ቤት ቤተ-መጻሕፍት ሄደ። የቆዩ ጋዜጦችን ጠየቀ።

ስለሪፑብሊኩና ስለንጉሠ-ነገሥቱ ግዛት ታሪክና ስለሴንት ሄለና የተጻፉትን ብዙ አነበበ። ጋዜጣን፤ መጽሔትንና መጻሕፍትን አገላበጠ። ስለታላቁ ጦር ሠራዊት ባነበበ ጊዜ የአባቱ ስም ከዚያ ተጠቅሶ አየ። አባቱ ጀርጅ ፓንትመርሲ ከየትኛው ጀኔራል ጦር ስር እንደነበረ ሲፈልግ ከጀኔራል ማብዩፍ ቸርችዎርደን ጦር ስር እንደነበር ደረሰበት። ጀኔራሉ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያገኛቸው ሽማግሌ እንደሆኑ አወቀ። እየተመላለሰ ጠየቃቸው። ጀኔራሉ ስለአባቱ የጦር ሜዳ ጀብዱ፤ ስለሚሸጠው አበባ፤ ስለብቸኝነቱ ብዙ ነገሩት። ማሪየስም ስለዚህ ተንኖ ስለጠፋውና ስለተረሳው ጀግና አባቱ ብዙ ተማረ።

በጀመረው ምርምር ብዙ ስለተዋጠ እነመሴይ ጊልኖርማንድን ረሳቸው። ብዙ ጊዜ አይገናኙም። የሚተያዩት በገበታ ጊዜ ብቻ ሆነ። ሲፈልጉት አያገኙትም፤ «አሁን ወጣ» ይባላል። አክስትየው ማጉረምረም ጀመረች። አያት ፈገግ አሉ «አባክሽ ተይው፤ ከሚያቅበጠብጥ እድሜ ላይ ስለሆነ ነው» ይላሉ። አንዳንድ ጊዜ ግን «ይኼ ሰይጣን! ሙያ ያለው ነገር የሚሠራ መስሎኝ ነበር፤ ለካስ ለስሜቱ ነው ተገዥ የሆነው» ብለው ይናገራሉ።

እውነትም የስሜት ተገዥ! ማሪየስ ስሜቱ አስገድዶት የአባቱ ተገዥ ሆነ። በአንዳኝ ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የአመለካከት ለውጥ አደረበት። ቀስ እያለ በፊት የነበረው አሳብ በሌላ ተቀየረ። የአስተሳሰብ አድማሱ እየሰፋና እየተለወጠ መሄዱ ታወቀው። ይኸው ነው፤ ብዙ ነገር ባጋጠመን ቁጥር የአስተሳሰብ ይዘታችንን ደረጃ በደረጃ መልኩን እየቀየረ ይሄዳል።

የሚያነበው ታሪክ አስገረመው። በመጀመሪያ ነገሩ ሁሉ ተምታቶበት ነበር። ሪፐብሊክ ወይም የንጉሠ-ነገሥት ግዛት ማለት ለእርሱ ዝም ብሎ ቃላት መስለውት ነበር። ስለሁለቱ የአስተዳደር ዘይቤዎች ባነበበ ቁጥር በይበልጥ ይገረማል። አንዳንድ ጊዜ ያለበት ይጠፋዋል። ቀስ በቀስ የመደነቁና የመገረሙ ነገር እየጠፋ ነገሮችን በግልጽ ወደማየትና ወደማመኑ አዘነበለ። አርእስተ-ጉዳዮችን ያለ ስህተት መተንተን ቻለ። አብዮትና የንጉሠ-ነገሥት

አገዛዝ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ቁልጭ ብሎ ታየው። ሰዎች ራሳቸውን እንዴት እንደሚከፋፍሉ ታወቀው። እውነተኛ ሪፑብሊክ የሰዎች መብት ሳይከበረውና የንጉሠ ነገሥት አገዛዝ ማክተሚያ መሆኑን ተረዳ። «ይኸማ ጥሩ ነው» ሲል አሰበ።

በጣም ተጸጸተ። ራሱንም ወቀሰ። አባቱ በሕይወት ቢኖርና ሊያገኝው ቢችል ወይም በአንድ ዓይነት ተአምር ከተቀበረበት ነፍስ ዘርቶ ቢነሣ እንዴት አድርጎ ወደ አርሱ በርሮና ሮጦ ሄዶ በማልቀስ «አባዬ! መጣሁልህ! እኔ ልጅህ ነኝ! የእኔ ልብ እንዳንተው ልብ ነው!» ቢለው ምንኛ ደስ ባለው። ይህ ቢሆን ያቅፈዋል፤ ይስመዋል፤ ፀጉሩን በእንባ ያርስለታል፤ ከፊቱ ላይ የነበረውን ጠባሳ ያሻሽለታል፤ እጆቹን ጥብቅ አድርጎ ይይዛል፤ ልብሱን ይነክሳል፤ ጫማውን ይስማል።

ለምን አባቱ ያለ እድሜ ይሞታል? ትክክለኛውን ፍርድ ሳይቀበል ልጅ ፍቅር ሳይረካ ለምን ቶሎ ሞተ? ማሪየስ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። አውቀቱ እየጎለበተና እምነቱ እየጠና ሄደ። ለአባቱና ለአገሩ ያለው ፍቅር እውነቱ ውስጥ ሠርጾ ገብቶ አንገበገበው። በየደቂቃው እውነት እየጎላ መጦ የአስተሳሰቡን አድማስ አሰፋለት። በመንፈስ ያደገ መሰለው።

አንድ ቀን ማታ ሻማ አብርቶ መጽሐፍ እያነበበ ከክፍሉ ውስጥ ቸውን ቁሙ ይላል። የነበረበት ክፍል መስኮት ተከፍቶአል። ብዙ ዓይነት ከር ከሞንቅላቱ ውስጥ ገብቶ አሳቡን አመሰቃቀለበት። ሌሊት ሌሊት እኮ ከት ነገር ይታያል! የሚርመሰመስ ድምፅ ይሰማል፤ ከየት እንደሚመጣ ግ አይታወቅም። ካለንበት ምድር አንድ ሺህ ሁለት መቶ ጊዜ የምትልቀው ፔተር እንደ ቁርበተ-አሊም እያበራች ማታ ማታ ነው የምትታየው። ማታ ማታ ከዋክብት ይብለጨለጫሉ፤ ሌሊት ደግሞ የፍርሃት መስፈሪያ ነው።

❄❄❄

ማሪየስ በመጨረሻ ስለናፖሊዮን ጦር ሠራዊት ነበር የሚያነብበው። ሚያነብበው መጽሐፍ አልፎ አልፎ የአባቱ ስም ተጠቅሶ ያያል። የንጉሠ ም ግን በየምዕራፉ ይጠቀሳል። አገሪትዋ በሙሉ ለንጉሠ እንደተሠራች ትኗን ነበር ጽሑፉ የቀረበው። እንደ ማሰበል ከውስጥ አካሉ አንድ ነገር ሊያቅየ ተሰማው። አባቱ በአጠገቡ አልፎ በሹክሹክታ ያነጋገረው መሰለው። ሸበር፤ የመድፍ፤ የመለከት፤ በሩቁ የሚሰማ የሠራዊትና የፈረስ ኮቴ

ከፊቱ ድቅን አሉ። ማንበቡን ትቶ በመስኮት ወደ ሰማይ ተመለከተ። የሚያብለጨልጭ ነገር ከሰማይ ተወርውሮ የሚያነብበው መጽሐፍ ውስጥ የወደቀ መሰለው። ፍርሃት፤ ፍርሃት አለው። የሚተነፍሰው በግድ ሆነ። ሰውነቱ ራደ። ማን እንዳዘዘው ምን እንዳስገደደው ሳይታወቀው ከተቀመጠበት ብድግ አለ። ወደ መስኮቱ ሄዶ እጆቹን ወደ ውጭ ዘረጋ። በጨለማ ሰማዩንና ምድሩን በዓይኑ ማተረ። ዓለም ጸጥ-ረጭ ብላለች። በድንገት «አድሜ ለንገሠ ነገሥቱ» ሲል ጮኸ፤ በማፌዝ።

ከዚያን አለት ጀምሮ ማሪየስ ጨርሶ ተለወጠ። ለአባቱ ንጉሠ ነገሥቱ እንደ ተወዳጅ ካፕቴን እንደነበሩ ተገንዘበ። ተወዳጁን ካፕቴን ያደንቅና ለእርሱም ሕይወቱን አሳልፎ እንደሰጠ ታወቀው። ለማሪየስ ናፖሊዮን ማለት ግን ከዚህ የበለጠ ነበር። የወደፊት ተስፋ፤ የድምበር መከታና የፊረንሳይ አለኝታ ከናፖሊዮን ቦናፓርቴ ላይ አየ። ናፖሊዮን ጨካኝ ሊሆን ይችላል። ግን እርሱ መታየት ያለበት ከሪፑብሊክ ምስረታ፤ ከለውጥ፤ ከአብዮት ጋር ነው። ናፖሊዮን የሕዝብ ሰው እንደሆነ አመነ። አባቱ ጦር ሜዳ የተዋጋውና ሕይወቱን አሳልፎ የሰጠው ለሰዎች እኩልነትና ለሪፑብሊኩ ምሥረታ እንደሆነ በፍጹም ልቡ ተቀበለ። የዚህ ተቃዋሚ የሆነውን የቡርቫን አገዛዝ ጠላ።

አያቱ መሴይ ጊልናርማንድ የሚደግፉት እርሱ የጠላውን ነበር። በዚህ የተነሣ በአያትና በልጅ ልጅ መካከል አለመግባባት ተፈጠረ። ከነአካቴው አያቱ ከአባቱ ጋር ያለያዩት በዚህ መሠረታዊ የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት እንደሆነ በተገነዘበ ጊዜ አያቱን በጣም ጠላቸው። በዚህ በግል ጥቅም በታወሩ ሰው ምክንያት ርህራሄ በተለየው ጭካኔ ልጅ ሊያፈቅረው ከሚችል አባቱ፤ አባት ከሚወደው ልጁ መለያየታቸው እጅግ በጣም አሳዘነው። ማሪየስ ከአባቱ ጋር የተለያየው በዚህ ምክንያት መሆኑን ባወቀ ጊዜ ለአባቱ ያለው ፍቅር ሲገነፍል ለአያቱ የነበረው ጥላቻ ማን ከደሙ ጋር ተቀላቀለ። አባቱ ማለት ለሰዎች ደኅንነት፤ ለሰዎች እኩልነትና ለትክክለኛ ፍርድ የቆመ ታላቅ ሰው ማለት ሲሆን፤ መሴይ ጊልናርማንድ ማለት ደግሞ በግል ጥቅም የታወሩ፤ ለጥቂት ሰዎች ደኅንነት ጥብቅና የቆሙና እንደ መኾነገር በሰዎች ደም የሰቡ ሰው ናቸው። ስለዚህ ቅራኔያቸው የሚታረቅ አልሆነም። ይህም የአያቱን ዓይን ላለማየት አስመሰለው። ሰዠብ አስባብ እየፈጠረ ከቤት ይጠፋ ጀመር። አክስቱ ድንገት አግኝተው የት እንደነበር ሲጠይቁት «ጥናት በዝቶብኝ ከጓደኞቼ ጋር ሳጠና፤ ፈተና ስለነበረብኝ ከአንድ ጓደኛዬ ቤት ውስጥ ተዘግተን ስናጠና፤ ፍርድ ቤት ሄደን ስለፍርድ አሰጣጥ ትምህርት ስንቀስም፤ አሁን ትምህርቴን ወደማጠናቀቁ ስለሆነ የመመረቂያ ጽሑፍ መጻፍ ስለጀመርሁ ቤተ-መጻሕፍት ውስጥ ስለምውል» አያለ ሌላም፤ ሌላም መልስ ይሰጣቸዋል።

አያቱ ግን «ማሪየስ ፍትሮ ያሁት ፍትረኛው አያንከራተተቸው ነው» ብለው መደምደሚያ ላይ ስለደረሱና አርሳቸውም በዚህ ዓይነት ገጠመኝ ያለ ስለሆነ ብዙም አልተፈጠነቱበትም። ሆኖም ማሪየስ እንኳን ቀን ሲገባ ፊርም የሚመጣበት ጊዜ በረከተ።

አንድ ቀን «የት ሊሄድ ይችላል?» ሲሉ አክስቱ ጠየቁ።

ማሪየስ አባቱ በጻፈለት ማስታወሻ መሠረት ቲናርዴን ለመጠየቅ ጁ ምንትፌርሜ ሄዶአል። ከዚያም የቀድሞውን የዋተርሉ ሃምሣ አለቃ፤ ጄው የሆቴል ቤት ጌታ ሚስተር ቲናርዴ ከስሮ ሆቴል ቤቱ ስለተዘጋ ጊዜው አራት ቀን ወስደበት።

«እርግጥ ፊሩን እየለቀቀ ነው» አሉ አያቱ እንደዚያ ሲቆያ።

ሚስተር ጨርቅ የተንጠለጠለ አንድ ነገር ከሸሚዙ ስር ከአንገቱ ላይ ጎትቶ አባትና ልጅ ቀደም ሲል ማየታቸውን አንስተው ተወያዩ።

ማሪየስ ለመጀመሪያ ጊዜ ከፓሪስ ከተማ ሲጠፋ የሄደው ወደ ቬርኖን ነው። ቬርኖን ከተማ ሄዶ በጠፋ ቁጥር አያቱ «ተኝቶ ነው» ይላሉ።

አንድ ቀን ጠዋት ማሪየስ ከቬርኖን ተመልሶ ከቤት ሲገባ አያቱ ሟቻቸው ነው። ከሁለት ቀን የአሳብ ጭንቀትና መንገድ በኋላ ስለነበረ ሁኔታ ከአልጋው በጣም ደክሞታል። ብዙ እንቅልፍ ስላላገኘ ቶሎ ብሎ ለአንድ ሰዓት አንኳን ቢሆን ለመተኛት ይፈልጋል። ኩቱንና አንገቱ ላይ ያጠለቀውን ጥቁር አውልቆ አልጋው ላይ ወረወረ። እንዳይረበሽ ከመዋኛ ሥፍራ አጠገብ ከሚገኝ ክፍል ውስጥ ለመተኛት ፊልጎ ወደዚያው ሄደ። ጤነኛ የሆኑ ሰዎች በጠዋት መንቃታቸው የተለመደ ስለሆነ መሴይ ጊልናርማንድ ሆነ አሉት በጠዋት በመንቃታቸው ማሪየስ ከውጭ ሲገባ ሰሙት። ጫጫታው ተነስተው በሽማግሌ እግር ቶሎ ቶሎ በመራመድ የማሪየስ ክፍል ቤት ወደነበረበት ክፍል ወደ ፎት ወጡ። የወጡት ሊያቅፉና ሊስሟት፤ በዚያውም ከየት እንደሚመጣ ሊጠይቁት ነበር። ግን ከክፍሉ ሲደርሱ ማሪየስ አልነበረም። አልጋው እንደተነጠፈ ነው። ኩቱና አንገቱ ላይ የሚያንጠለጥለው በጥቁር ሪበን የታሠረው ነገር ከአልጋው ላይ ተጥሎዋል።

«ይህቺ ጥሩ ናት» አሉ መሴይ ጊልናርማንድ።

ልጃቸው ወደ ነበሩበት ወደ ምድር ቤት ሳሎን ወረዱ። እህትየው ትኩት ኖሮ ከሳሎን ቤት ቁጭ ብለው ጥልፍ ይጠልፋሉ። መሴይ ጊልናርማንድ በአንድ እጃቸው የማሪየስን ኮት በሌላ እጃቸው አንገቱ ላይ ያንጠለጠለውን ነገር ይዘዋል።

«ድል ይሉኻል ይኸ ነው፤ ምስጢሩን ሳንደርስበት አንተርም መፈኔረሻውን እንደርስበታለን፤ ይኸውልሽ ጉዳ» ሲሉ ሮሙ፤ ልጃቸው ከነበሩበት ክፍል እንደገቡ።

በራበን የተንሰፈሰፈው ነገር የሳጥን ትረጽ ያለውና የሚከፈት ነው። ሽማግሌው ላይከፍቱት አተኩረው ተመለከቱት።

«አባባ፤ ክፈተውና እንየው» አለች ልጃቸው።

ሳጥኑን ጫን ሲሉት ይከፈታል። በውስጡ ያገኙት ከብጣሽ ወረቀት ጋስተቀር ሌላ ነገር አልነበረም።

«ከአንድሞ ፍቅረኛው ጠፍ ሊላሞ» አሉ መሲይ ጊልናርማንድ በኃይል እየሳቁ። «ምን እንደሆነ አውቀሞለሁ፤ የሳቅር ደብዳቤ!»

«ይሆናል፤ ይነበባ!» አለች የማሪየስ አክስት።

መነጽርዋን አደረገች። ወረቀቱን በረጋጋችና አነበበች።

«ለምወድህ ልጄ፤ ዋተርሉ ጦር ሜዳ ላይ በተዳረገው ጦርነት ስለፈጸምኩት ጀብዱ የባሮንነት ማዕረግ ተሰጥቶኝ ነበር። ማዕረጉን በደግ የዋጀሁት ስለሆነ ለልጄ ማውረስ እችላለሁ። እኔ አሁን ማዕረጉ ይገባዋል ወይም አይገባውም ብዬ መናገር የለብኝም።»

የአባትና የልጅ ፊት እንዴት እንደተለዋወጠና ስሜታቸው ምን እንደነበር መግለጽ ያዳግታል። የሚሞት ጥላ እንደተጋረደበት ሰው በብሽቀት ደነዘዙ፤ አብድ ሆኑ። በንዴት ሰከኑ። ዝም ዝም ተባባሉ። በመጨረሻ መሲይ ጊልናርማንድ እርስ በራሱ እንደሚናገር ሰው እጅግ ዝት ባለድምፅ ተናገሩ።

«የዚያ ጦረኛ የእጅ ጽሑፍ ነው።»

«አክስቱ ጽሑፉን እገላብጣ መረመረችው። አገላብጣ ካሆችው በኋላ ከሳጥኑ ውስጥ መልሳ ከተተችው። እርስዋ ወረቀቱን ስትጨምር ለሳ ሰማያዊ ቀለም ያለው ወረቀት ከማሪየስ ኮት ኪስ ወደቀ። ብድግ አደረገችው እንድ መቶ የግል ካርዶች ነበሩ። አንዱን ለመሲይ ጊልናርማንድ ሰጠቻቸው ከካርዶቹ ጀርባ ባሮን ማሪየስ ፓንት መርሲ የሚል ጽሑፍ ተጽፎበታል።

ሽማግሌው ደወል ደወለ። አሽከር ገባ። ሪሰኑንና ሳጥን መሳዩን ነገር እንዲሁም የማሪየስን ኮት ከመሬት ከወረወርዋቸው በኋላ «ከዚህ አጥፋልን» ሲሉ ተናገሩ።

አንድ ሰዓት ሙሉ በዝምታ አለፈ። አባትና ልጅ ጀርባ ተሰጣተኮ ዝም ተባብለው ተቀመጡ። ምናልባት ስለተመሳሳይ ነገር ሳያስቡ አልቀሩም

አንድ ሰዓት በኋላ የማሪየስ አክስት «ይሁና፤ ደህና ነዋ!» ስትል ተናገረች።

ወዲያው ማሪየስ ሰምቷ ከነበሩበት ክፍል ገባ። ከሳሉኑ እንደገባ ከተመው ካርድ አንዱን አያቱ ይዘውት ተመለከተ። የማሪየስ ወደ ሳሉን ፊባት ሽማግሌው ባዩ ጊዜ «ቱም! ቱም! ቱም! አሁን እኮ አንተ ባሮን ነህ። ነሺን ደስ ያለህ አልሃለሁ። እስቲ ይህ ምን ማለት እንደሆነ አስረዳን?» ሉት ተናገሩ።

ማሪየስ ጥቂት ድንጥ ቢልም ሰተጠየቀው ጥያቄ መልስ ሰጠ።

«ትርጉሙማ እኔ የአባቴ ልጅ ነኝ ማለት ነው» አለ።

«አባትህ! አባትህማ እኔ ነኝ» አሉ መሲይ ጊልናርማንድ

«አባቴ» አለ ማሪየስ በመደንገጥ የመሲይ ጊልናርማንድን ዓይን አተር ብሎ እያየ፤ «አባቴ ሪፑብሊኮንና ፈረንሳይን ያለገለ ጀግና ሰው ነር። ስሙ ከጀግኖች ታሪክ ማጎደር ውስጥ ተጽፎ ይገኛል። የአገሩን ሶማር ላለማስደፈር ለሃያ አምስት ዓመታት የቀን ወሐይ፤ የማታ ቁር ሂበግረው ቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ ኖሮአል። የአገሩን ነብር ለማስጠበቅ ለየጋ ከሃያ ቦታ ላይ ቆስሎአል። ሆኖም ለአገሩ የሰጠው አገልግሎት ተረስቶ እንዳልሆነ ሆኖ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። አባቴ የፈጸመው ስህተት ኒናር ሁለት ነው። እነርሱም አገሩንና እኔን ከመጠን በላይ መውደዱ ናቸው።»

ይህ አነጋገር የመሲይ ጊልናርማንድ ሕሊና ሊቀበለውና ሊያደምጠው ሚችል አልነበረም። ገና ሪፑብሊክ የሚል ቃል ሲሰሙ ከመቀመጫቸው ጀግ አሉ። ራሳቸው «የንጉሠ ነገሥቱ ወገን ነኝ» ብለው ስለሚያምኑ ማሪየስ እፍ የወጣው እያንዳንዱ ቃል እንደ ጦር እየወጋ ፊታቸውን ክከመው።

«ማሪየስ» ሲሉ ጮሁ። «አንተ ትፋታም! አባትህ ምን እንደነበር ዛወቅም፤ ለማወቅም አልፈልግም። ስለእርሱ የማውቀው ነገር የለኝም። ሕትኔንም አላውቅም። የማውቀው ነገር ቢኖር በእንድ ወቅት ርባነቢስ ሸኑ ዋቂት ሰዎች እንደነበሩ ነው። እነሱም ቢሆኑ ሁሉም ለማኞች፤ ኦሲንጓዎች የሚሊቱር ፖሊሶች፤ ሌቦች ነበሩ። ሁሉም ሀብም ነው ሾለው። ከዚህ የተለዩ አልነበሩም። ከዚህ የተለየ እኔ ማንንም አላውቅም። ሕትም ነው የምለው። ማሪየስ፤ ስማህ? አንተ ብሎ ባሮን! አንዚያ ዥቶች፤ ተማኞች፤ አታላዮች፤ አታላዮች፤ አታላዮች አውነተኛውን ነጥሎ ጅተው በሃንቮርቱን የተከተሉ ፈረሶች፤ የፈረ ፈረሶች ናቸው። ዋተርሉ ቲ ጠላቶችን ፈርተው የሸሹ ወሮበሎች፤ ይኸ ነው እኔ የማውቀው። ሕትህ ከዚህ ውስጥ ከሆነ አገኘለሁ፤ አላውቀውም ብል ይሻላል።»

መሴይ ጊልናርማንድ በታላት ወናፍ ሲያራግቡት ማሪየስ በተራው ጮሰ፤ ተናደደ፤ ቁጣው ገነፈለ። ሰውነቱ ተንተበተበ። የሚያደርገውን አጣ፤ የሚናገረውም ጠፋው። የአባቱ ስም ከፊቱ ተረገጠ፤ ተናቀ። በማን? በአያቱ። ታዲያ እንዴት ይበቀል? አያቱን መልሶ አንዳይሰድብ ያስነውራል። ዝም እንዳይልም አሳቡ ዘገነነው። በአንድ በኩል የአባቱ መቃብር በሌላ በኩል የአያቱ ሽበት ታየው። ነገሩ ሁሉ ስለተምታታበት ፈዘዘ ቀረ። ጥቂት ቆይቶ ቀና በማለት አያቱን አፍጥጦ አያቸው።

«በርበሬችና ትልቁ አሳማ ልዊ 18ኛ ይውደመ» ሲል በታላቅ ቁጣና ጩኸት ተናገረ።

ንጉሡ ልዊ 18ኛ ከሞቱ አራት ዓመት አልፎአል። ግን ለማሪየስ ለውጥ አላመጣም።

ሽማግሌው በድንገት ፊታቸው በንዴት ብዛት ከወጉራቸው ጀምሮ ጠቆረ። ከዚያም ቃል ሳይናገሩ አንዱ ወደ መስኮት፤ አንዱ ወደ በሩ በዝግታ ተራመዱ። ቀጥሎም እንዳረጀ በግ ድምብርብራቸው ወደ ወጣው ሴት ልጃቸው ዞር ብለው ፊገግ በማለት የሚቀጥለውን ተናገሩ።

«እንደ መሴይ ያለ ባሮን እንደ እኔ ያለ ቡርኝቮዋ ከአንድ ጣራ ስር ለማኖር ያዳግታል።»

ሰውነታቸው እየተንቀጠቀጠና ቁጣቸው እንደነበልባል ከፊታቸው ላይ እየበራ ቀጥ ብለው ቆሙ። እጃቸውን ወደ ማሪየስ ዘርግተው «ከዚህ ቤት ውጣልኝ» ሲሉ ጮሁ። ማሪየስ ከቤቱ ወጣ።

በሚቀጥለው ቀን ለሴት ልጃቸው ሲናገሩ «ለዚህ ደም መጣጭ በየስድስት ወር ስልሣ ፒስትልስ ትልኪለታለሽ፤ ስለእኔ ግን ሁለተኛ ምንም ነገር እንዳታነሺ» ሲሉ አዘዙ።

ነገሩ በጣም ስላሳዘናቸውና ስላናደዳቸው በሚቀጥሉት ሦስት ወራት የሚይዙትንና የሚጨብጡትን አላጣቸው። ሴት ልጃቸውን ሲያነጋግሩ እንኳን እጅግ ቀዝቀዝ ብለው ነበር።

ማሪየስ ከቤቱ የወጣው ወደዚያ ቦታ ነው የምሄደው ሳይል ነበር። እነርሱም የት እንደሚሄድ አልጠየቁትም። ጋሪ ተከራይቶ ዘልሎ ከገባ በኋላ ጋሪው ወደ መራው ሄደ።

ማሪየስ ምን ሊያደርግ ነው?

ምዕራፍ ሰሥራ አምስት

የእህቤሴ ጓደኞች

ማሪየስ ከቤቱ በወጣበት ጊዜ የለውጥ አየር ይነፍስ ነበር። ሰው ሁሉ ሀሳቡ ንቅናቄ ውስጥ እየገባ አብዮተኛ ሆኖአል። እያንዳንዱ ግለሰብ ሀገሪቱ እርምጃ ወደፊት ተራመደ። ንጉሣውያን ቤተሰብ እንኳን ሳይቀሩ በጭፍጨፋ ላይ ነው። ሰዎች ከጊዜ በኋላ ናፖሊዮንንና ነፃነትን እንደ አምላክ የማምለክ ያህል አደረባቸው። ሌሎች ደግሞ ዓለም ፍጹም እንድትሆን ተመኙ። ይህው ምኞት ነገ ሥጋና ደም ለብሶ እሙን እንደሚሆን አመኑ።

የእህቤሴ ጓደኞች እነማን ናቸው? እህቤሴ የተረገጡ፤ የተከፉና ሥራ ዋቁኖች ሲሆኑ እነዚህ ሰዎች በፖለቲካው እንቅስቃሴ ላቢያ ብዙ ያደሩ ያፈሩ ናቸው። ጓደኞቻቸውም ከወደቁበት እንዲነሱ ክልብ ጥረዋል። ሰዎቹ ብዙ አልነበሩም። ፓሪስ ከተማ ውስጥ ሃሌሱና ኮርኒት ነዳሱ ሥፍራዎች በየጊዜው ከአንዲት አነስተኛ ቡና ቤት ውስጥ ይሰበሰቡ። ሥፍራው ወዛደሮች የሚኖሩበት አካባቢ ነው። በዚያ አካባቢ ሚኖሩም በብዛት ይገኛሉ። የእህቤሴ ጓደኞች የሚሰበሰቡበት ቡና ቤት «ሚ ሙሴን» ይባላል። ቡና ቤቱ ሰፊ ጓዳ ስለነበረው የእህቤሴ ጓደኞች ሀ ክፍል ውስጥ ይሰበሰባሉ። ክፍሉ ከዋናው መጠጫ ክፍል ትንሽ ራቅ ነ ነበር። በጓሮ በኩል ወደ ውጭ የሚያስወጣ በር አለው።

ጓደኞቹ ከዚያች ክፍል ውስጥ ይጠጣሉ፤ ሲጃራ ያጬሳሉ፤ ያወጋታሉ፤ የፖለቲካ ወሬ ያወራሉ። የማያነሱት ነጥብ የለም። ከክፍሉ ጀነዳ ላይ የበፊቱን የፈረንሳይ ሪፑብሊክ ካርታ ሰቅለዋል።

የዚህ ቡድን አባሎች አብዛኞቹ ተማሪዎች ሲሆኑ ጥቂት ወዛደሮችም ነበት። ጥቂት ቀንደኛ መሪዎች አሉዋቸው። ከመሪዎቹ መካከል ነጂልራስ የተባለው የሀብታም ልጅ ቀንደኛ መሪ ሲሆን ደስ የሚልና ጭ መልካም ወጣት ነው። ደግሞም በጣም አዋቂ ከመሆኑም በላይ ጌ ለጉድ ነው። ከቀንደኛው መሪ ከኢንጀልራስ ጎን የተሰለፉ ሌሎችም ጽ መሪዎች አሉ። አንዳንዶቹ በፖለቲካው ሌሎች ደግሞ በስሙ ልጅ ቂ የሰከሩ ናቸው። አንዳንዶቹ «ጭቁኖችን ነፃ እናወጣለን» ብለው ሌ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ «አገራችን ውስጥ አድልዎ የተለየው ትክክለኛ ርት እንዲሰፍን ጽኑ እምነታችን ነው» የሚሉ ናቸው።

ሆኖም በመካከላቸው አንድ ተጠራጣሪ ሰው ነበር። ታዲያ የሕዝቦችና ነፃነት መብት፤ የፈረንሳይ አብዮት፤ ሪፑብሊክ፤ ዲሞክራሲ፤ ሰብአ ነ፤ ሥልጣኔ፤ ሃይማኖት፤ መሻሻልና የመሳሰሉት ቃላት ለእርሱ

ትርጉም የላቸውም። እነዚህን ቃላት በስማ ቁጥር ይስቃል። ፡ዲያ ከነዚህ የተለየ ዓላማ ነላቸው ስምት መከክል ይህ ሰው እንዲት ሊደባለት ቻለ?

ይህ ሰው ተጠራጣሪ ቢሆንም የራሱ አምነት ነበረው። አምነቱ በኢንጀልራስ ላይ ነው። ኢንጀልራስን ይወደዋል፤ ያደንቀዋል፤ ያምንበታል። ለዚህ ነው በዓላማ አንድ ከነበሩና እንደ ቤተሰብ ከሚተያዩ ሰዎች መከከል ሊገባ የቻለው። ኢንጀልራስ ይህን ተጠራጣሪ በፍልስፍና ወይም በነበረው የተለየ አሳብ ሳይሆን በጠባዩ ነው የገዛው።

አንድ ቀን ከስዓት በኋላ፤ ሕይወት በኢጋጣሚ የተሞላች ናትና፤ አንድ ነገር በኢጋጣሚ ይሆናል። ከፈረንሳይ አብሮት ከንሳሰች መከከል አንዱ ከካፌ ሙሴን በራፍ ግድግዳ ተደግፎ ቆሞአል። እርሱ ከዚያ እንደቆመ ጋሪ በዚያ በኩል ያልፋል። ይህ ሌግል የተባለ ወጣት ጋሪውን ሲመለከተው በጣም ዝግ ብሎ ስለሚሄድ አንድ ነገር እንደሚፈልግ ጠረጠረ። አነስተኛ ሻንጣ የያዘ ሰው ጋሪው ላይ ከነጂው ጎን ቁጭ ብሎአል። ሻንጣው ላይ ማሪየስ ፓንትመርሲ የሚል ጽሑፍ በጉልህ ተጽፎበት ስለነበር ሌግል ጽሑፉን ያነባል።

ማሪየስ ፓንትመርሲ የሚለው ስም በጣም ማረከው። ጋሪው ከአጠገቡ ሲደርስ «መሴይ ማሪየስ ፓንትመርሲ» ሲል ተጣራ። ጋሪው ቆመ። ጋሪው ላይ የነበረውና በአሳብ መጥቆ ሄዶ የነበረው ወጣት ቀና አለ።

«ምን ነበር?» ሲል ጠየቀ።

«መሴይ ማሪየስ ፓንትመርሲ ማለት አንተ ነህ?»

«ነኝ።»

«ስፈልግህ ነበር።»

«እንዴት ሊሆን ይችላል? አታውቀኝ፤ አላውቅህ» ሲል ማሪየስ ጠየቀው።

«ትናንት ትምህርት ቤት አልመጣህም።»

«ላልመጣ እችላለሁ።»

«በርግጥ አልመጣህም።»

«ተማሪ ነህ አንተም?»

«አዎን፤ እንዳንተው ተማሪ ነኝ። ከትናንት ወዲያ ልክ ወደ ከፍል ልገባ ስል፤ አለ አይደል አንዳንዴ አስተማሪዎች ሦስት ጊዜ ስምህን ሲጠሩ አቤት ካላልክ ይሠርዝሃል። ስልማ ፍራንክ ቀለጠች ማለት ነው።»

ማሪየስ ዝም ብሎ ይሰማል። ሌግል ንግግሩን ቀጠለ።

«ሁለንዳው የሚባለው አስተማሪ ነበር ስም የሚጠራው። አስተማሪውን ታውቀዋለህ አይደል? ያ እንኳን ቀፋፊና ግትር አፍንጫ ያለው! የቀረ ላቹ የመዘገበ እንደሆነ ደስታው አይጣል ነው። ስም ሲጠራ ሁለም ነት ስለለ በጣም ተከፋ። ብሉንዳው ዛሬ የሚቀጡት ሰው ስላላገኙ ው፣ የኔ ፍቅር አልኩ በልቤ። በድንገት ወዲያው ማሪየስ ፓንትመርሲ ይ ይጣራል። ድምፁን ከፍ አድርጎ እንደገና ማሪየስ ፓንትመርሲ ሲል ብሉንዳው አልኩኝ በልቤ። ብዕሩን እንዳነሣ ለሦስተኛ ጊዜ ማሪየስ ትመርሲ ሲል ተጣራ። እኔ እንዳቀረቀርኩ 'አቤት' ስል መለስኩለት። ም ከመሰረዙ ዳነ።»

«ፈታው...!» አለ ማሪየስ።

«ፈታማ ነበርኩ» ሲል ለሌግል መለሰ።

«አልገባኝም» አለ ማሪየስ።

ሌግል ወሬውን ቀጠለ።

«ስሜ ሌግል ይባላል።»

«ሌግል፤ ደስ የሚል ስም ነው» አለ ማሪየስ።

«አቤት ብዬ ስመልስ አስተማሪው ነብር መስሎ ቀና ብሎ ያየኛል። ፓንትመርሲ ከሆንክ እንግዲያው ሌግል አይደለህም ሲል ስሜን ጀው ውስጥ ፋቀው።»

«ምም አገናለሁ» ሲል ማሪየስ ጣልቃ ገባ። ሌግል ክት ብሎ ሳቀ።

«እኔ እንደሆነ ደስ ነው ያለኝ። አንተ ከገባህበት የሕማ ትምህርት ልገባ ጅ ኛ ትምህርቱን ልጀምረው ስል ይህ አጋጣሚ አዳነኝ። ስለዚህ በዚህ ነሚ አንተን ላመሰግን አንጂ! ለመሆኑ የት ነው የምትኖረው?»

«ጋረው ላይ» አለ ማሪየስ እንደማፌዝ ብሎ።

«ቡቴጃርንት ምልክት ነዋ!» ሲል ሌግል መለሰ። «እንኪን ደስ ያለህ። ጠ ዘመን ዘጠኝ ሺህ ፍራንክ ነው ለባለጋረው የምትከፍለው?»

ሌግል ይህን ሲናገር ንደኛው ኩርፌይራክ ከዙና ቤቱ ብቅ አለ። የመገረም ፈገግታ አነሃ።

«ጋረው ሳልወርድ ለሁለት ሰዓት ያህል ተንቀዋልያለሁ። አሁን ቢቀኝ ይሻላል። የት እንደምሄድ ግን አላውቅም ብል ለወጣቶች

አዲስ ነገር አይሆንም።»

«አይዞህ» አለ ኩርፌይራክ፤ «ከእኔ ቤት ልንሄድ እንችላለን።»

ያን አለት ወደ ማታ ኩርፌይራክ ከሚያርፍበት ሆቴል ማሪየስ አብሮ ሄደ።

❀❀❀

፱

በጥቂት ቀናት ውስጥ ማሪየስና ኩርፌይራክ በጣም ተቀራረቡ። በወጣትነት ዘመን ወዳጅ ማፍራት ቀላል ነው። ማሪየስ ጓደኛው ኩርፌይራክ እስካለ ድረስ ደስ እያለው በነፃነት ይኖራል። እንደፈለገው ነፃ ሆኖ መኖር ለእርሱ አዲስ ነገር ነበር። ኩርፌይራክ ጥያቄ በማብዛት አይነተርከውም፡ እነርሱ በደረሰበት የወጣትነት እድሜ ጉትርክ እንደሚጠላ ኩርፌይራክ ጠንቅቆ ያውቃል።

ኩርፌይራክ ማሪየስን ወደ ካፌ ሙሴን ይዞት ሄደ። ከዚያም ፊገሚ እያለ ወደ ጆሮው ጠጋ ብሎ «የንትናቱው አባል እንድትሆን የመግቢያ ፈቃድ አሰጥሃለሁ» ሲል አንሾካሾከለት። የአብዬሱ ጓደኞች ከሚሰበሰቡበት ክፍል ወሰደው። ከሌሎች አባሎች ጋር «ተማሪ ነው» ሲል አስተዋወቀው። ለምን ተማሪ ነው ብሎ እንዳስተዋወቀው ማሪየስ አልገባውም።

የማሪየስ አስተዳደግ የብቸኝነት ሲሆን እንዲህ ዓይነቱን ግርግር አልለመደውም። ወጣቶች በብዛት ተሰባስበው እርስ በእርስ ሲፋጨሩና በእንደ ላይ ሲወያዩ ለእርሱ አዲስ ነገር ነው። አንዳንድ ተሰፈንጣሪዎች በነገር ስለሚነካኩ በመጠኑም ቢሆን ይደናገረዋል። እነዚያ ወጣቶች ሁሉ በነፃነት እንደዚያ ሲወያዩ ገረመው። አንዳንዱም ከመገረም አልፎ ይደነቃል። እነዚያ ወጣቶች በአስተሳሰብ በተለይም በፖለቲካ ጉዳይ መጥቀው ሄደዋል። ወጣቶቹ ስለፍልስፍናና፤ ስለሥነጽሑፍ፤ ስለታሪክ፤ ስለሃይማኖት፤ ስለሥነ ጥበብና ስለመሳሰሉት ነገሮች ሲወያዩ አልፎ አልፎ መከታተል ይሳነዋል። የአያቱን አስተሳሰብ ጥሎ የአባቱን በተከተለ ጊዜ ሁሉ ግጭት የሚደርስበት አልመሰለውም ነበር። ግን ባይናገረውም እንደዚያ አልሆነም። ቀደም ሲል የነበረው ማንኛውም አመለካከት ቀስ እያለ ይለወጥ ጀመረ። አንዳንዱም አሳብ እርስ በእርስ እየተጋጨበት ከግራ ወደ ቀኝ ያወዛውዘዋል። ይህም እስከ መሰቃየት አደረሰው።

ወጣቶቹ የሚፈሩት ወይም በነፃነት የማይወያዩበት ነገር አልነበረም።

እርሱ የማይወያዩበት ነገር እርሱን በጣም ያስፈራዋል። ስለንጉሡና እመቤቲቱን እያነሱ በነፃ ይወያያሉ።

ማሪየስ ከወዳጆቹ ውስጥ ገብቶ አሳብ የሰጠ እንደሆነ ራሱ ያስመዋል። አንድ ቀን ማታ የአብዬሱ ጓደኞች በሙሉ መጥተው ስብሰባ ይጀምራል። ትልቁ መብራት ስለበራ ክፍሉ ወለል ብሏል። አርእስት እየቀያየሩ ይወያያሉ። ወይይቱ ሲካሄድ ብዙ አይንጫጩም። ስለዋተርሉ ጦርነትና እናፖልዮን ወራ ሲነሣ ማሪየስ ሳያስበው በድንገት ብድግ ብሎ ንግግር ያደርጋል።

«እኔ አዲስ መጤ ነኝ፤ ሆኖም እስካሁን በሰማሁት በጣም ነው የሚማቸሁኝ። የት ነው የምናመራው? እኛ ማን ነን? እናንተ ለመሆኑ ሁሉን ናችሁ? ወጣቶች መስላችሁኝ ነበር። ታዲያ ወኔያችሁን ምን ሰለበው? ናፖሊዮንን ካላደነቃችሁ ማንን ልታደንቁ ነው? ከእርሱስ ይበልጥ መሪ ግነ ነው የምትፈልጉት? ያንን ትልቅ ሰው ካልወደዳችሁ ከእርሱ የተሻለ ግነ ልታመጡ ነው? ጓደኞቼ ስለእውነት ተናገሩ። ከእርሱ ይበልጥ ሰልሽብ የቆመ መሪ ከየት ሊመጣ ነው! ትልቅ መንግሥትና ታላቅ ጦር ለመፍጠር፤ እንደ አእዋፍ ሠራዊቱን በየተራራው ለማሰራጨት፤ ከባድ ጠላጦር ለማሠማራት፤ ለማጥቃት፤ ለማርበድበድ፤ አውሮጳ ውስጥ ብቸኛ ለመኖር፤ በታሪክ አምድ ከፍተኛ ሥፍራ ለማግኘት፤ ዓለምን ጉዟ ላይሆን ሁሉቱ ለማሸነፍ ከእርሱ ይበልጥ ታላቅ ሰው ማን አለ? ጀግና ይበልጥ የከበረ ነገር ምን ይገኛል?»

«ነፃ መሆን» አለ ከስብሰባው ተሳታፊ አንዱ። ማሪየስን ለጥ ብሎ እጅ ሰጠ። «ነፃ መሆን» በማለት የተጠቀሱት ቃላት አጥንቱን ሰርስረው ነው ያገቱት። ቀና ቢል መልስ የሰጠው ሰው ከነበረበት የለም። አንድ ሰው ቶሎ ሳይ አያለ ሲዘፍን ተሰማ። ዘፈኑ ስለጁለየስ ቄሣር የተዘፈነ ነበር። ማሪየስ ጭድ እናቴ» እያለ አዜመ። ኤንጀልራስ ከኋላ መጥቶ ትከሻውን መታ፤ ሰታ አደረገው።

«ወንድም፤ ውድ እናት ማለት እኮ ሪፑብሊክ ናት» አለው።

ማሪየስ ከሁለት አምነት መካከል ይወጠራል። የጥንቱን ጨርሶ ጀረሰው አላስወጣም፤ አዲሱም ከልቡ ውስጥ ሥር አልሰደደም። የትኛ ነን ያጠንክር? ከሁለት አንድ መምረጥ ቀላል አይደለም። ለመወሰን ከጨነቸው መንገድ የሚያሳይ መብራት ያሻል።

ማሪየስ ለመቀጠል፤ ወደፊት ለመራመድ፤ ለማሰብ፤ ለመመራመር ሳቱ ያስገድደዋል። ወደፊት በሄደ ቁጥር አባቱን የቀረበ ይመስለዋል። ሳቱ እምነት ለመራት ደግሞ አይፈልግም። ከአያቱም ሆነ ከጓደኞቹ ጋር

በአሳብ ተራርቋል። ወደ ካፌ ሙሌን መሄዱን አቆመ።

በሕይወት፤ ለማሰላሰል የማይፈልጉትን ነገር ለመገንጠላት አውጥቶ ለመጣል ያዳግታል። ይህም በመሆኑ ሁለት ተቃራኒ አሳቦች ከሕሊናው ሊወጡ አልቻሉም። አንድ ቀን ጠዋት የሚኖርበት ሆቴል ጠባቂ ከክፍሉ ይገባሉ።

«መሴይ ኩርፌይራክ ለአንተም ኃላፊ ነው?»

«አዎን»

«ግን ገንዘብ ያስፈልገኝ ነበር!»

«ኩርፌይራክ እንዲያነጋግረኝ ይንገሩት» አለ ማሪየስ።

ኩርፌይራክ መጣ፤ የሆቴሉ ጠባቂ ከክፍሉ ወጣ። ማሪየስ በዓለም ላይ የእኔ ነው የሚለው ዘመድ ወዳጅ እንደሌለው ለኩርፌይራክ ቀደም ብሎ ለመንገር ፈልጎ እንደነበር ገለጸለት።

«ታዲያ ምን ይሻልሃል?» ሲል ኩርፌይራክ ጠየቀው።

«እኔ እንጃ!» ሲል ማሪየስ መለሰ።

የማሪየስ አክስት የልብ ክፉት ስለሌላት ማሪየስ እንዲሉት ሆኖ ይኖር ይሆን ብላ በማጠያየቅ የት እንዳረፈ ትደርስበታለች። አንድ ቀን ማሪየስ ከትምህርት ቤት ሲመለስ አክስቱ የጻፈችለትን ደብዳቤ ያገኛል። ከደብዳቤው ጋር ስድስት መቶ ፍራንክ በፖስታ ታሽጎ ተሰጠው። ማሪየስ ገንዘቡን መልሶ ለአክስቱ ላከላት። ከገንዘቡ ጋር ለመተዳደሪያ የሚሆን ገንዘብ ራሱ ለማፍራት መቻሉን በመግለጽ ትህትና የተሞላበት ደብዳቤ ጻፈላት። በዚያን ጊዜ ኪሱ ውስጥ የነበረው ገንዘብ ግን ሦስት ፍራንክ ብቻ ነበር።

ገንዘቡን ለመመለሱ አክስቱ ለአያቱ አልነገረቻቸውም። አያቱ ቀደም ሲል ስለእርሱ ሁለተኛ እንዳታነሱብኝ ስላሉ የማሪየስን ወሬ ማንሳት አልፈለገችም። ማሪየስ አዲው ስለበዛበት ሆቴል ቤቱን ለቅቆ ወጣ።

❀❀❀

፫

ሕይወት ለማሪየስ አየከበዳቸ ሄደች። ልብሶቹን ሸጠ እስከመብላት የሚያደርስ ችግር ገጠመው። ችግሩ በጣም የጠናውና ጥም ውሉ ማደር

ሥራው የሚሸጠው ንብረት ሲያልቅበት ነበር። ደረቅ ዳቦ ጠፍቶ በባዶ ሆድ ሊተኙ፤ ጠኔ እንቅልፍ አላስወስድ ብሎ ቁልጭ ብለው ሲያነጉ፤ መሬት ጠፍቶ በጨለማ ሲተራመሱ፤ ማንደጃ ላይ እንጨት ወይም ከሰል ያጡ ብዙ ሲያንቀጠቅጥ፤ ያለሥራ ሌት ተቀን ሲቀመጡ፤ የወደፊት ተስፋ ሲጨልም፤ ሱሪ ከቂጥ ላይ ሲቀደድ፤ በጭቅትት የደለበና ቀዳዳ ያጣ ቆብ ሲያጠልቁ፤ የቤት ኪራይ ስላልከፈሉ በር ከውጭ ሲዘጋ፤ ሸሹ ላቢያ ሳረቤት ሲሳለቅ፤ ሀፍረት አንገት ሲያስደፋ፤ ሰው ሁሉ እንደለማኝ ሲቆጥር፤ የሚያዝን ቢገኝ ምስኪን እያለ ሲጠራ፤ ምሬት፤ ቁጭትና ንዴት ራስ ሲያዞር ነው የኑሮ ጉድ፤ የኑሮ መከራ የሚታየውና ሰው ምንጊዜም መጡ የሚባለው።

ማሪየስ ይህ ዓይነት ሁኔታ ሲገጥም ምን እንደሚኮን ከደረሰበት ኢኮኖሚ ትምህርት ቀሰመ። አንገት ከመድፋት በስተቀር ሌላ ምርጫ እንደሌለው አወቀ። ሆኖም የሚያሳዝነው የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲገጥም ሰው በተፈጥሮው የሚመኛቸው እንደክብርና ፍቅር የመሳሰሉትን ነገሮች ያጨልጋል። ነገር ግን በስውር ሕሊናው ልብሱ ስለተቀዳደደና ስላደፈ ሰዎች ሚያሸፋብት፤ ድሃ በመሆኑ ሰዎች የሚሳለቁበት ይመስለዋል። ማሪየስ ልጣትነት ዘመኑ ከዚህ ዓይነት ፈተና ውስጥ በመውደቁ ያደረገው ቦት ቁማ ማለቅና መቆሸሸ ዓይኑን ዘቅዘቅ አድርጎ ያያል። በአጠቃላይ ያለበትን ፅናቱ ያጨናል። ፈተናው ደካሞች ስማቸው የሚጠፋበት፤ ብርቱዎች ክፍረት ማቅ ተንነው የሚጠፉበት መሆኑን ይገነዘባል።

በፈተና ጊዜ ከፈተናው ለመውጣት በሚደረገው ጥረት ላይታወቅ ብ ጠቃሚ ነገር ይሠራል። ጉልህ ሆኖ የማይታይ ጉብዝና ይከሰታል። ሕይወት፤ መጥፎ አጋጣሚ፤ ብቸኝነት፤ መረሳት፤ ድኅነትና ሌሎችም ቡሮ ጦር ሚዳዎች ሲሆኑ እያንዳንዳቸው የተሰወሩ ጀግናዎች ናቸው። አንዳንዱም ከእውነተኛው የጦር ሜዳ ጀግና የላቁ ይሆናሉ።

በችግር አለንጋ ተፈትነው የሚወጡ ጀግኖች ጥቂቶች ናቸው። ኖም ለጀግንነታቸው ድንበር የለው። መከፋት ግላዊ ክብርን እንደሚነዝከዝ ሁሉ መጥፎ አጋጣሚም ጡት አጥብቶ ያሳድገዋል። «ችግር ብልሃትን ይፈጥራል» ይባል የለ።

ማሪየስ ያሳለፈው ሕይወት ከዚህ የራቀ አልነበረም። ቤቱን ራሱ ነው የሚወለውለው። ቀለቡን በብር ላይሆን በሳንቲም ነበር የሚገዛው። ቀለቡን ለመግዛት ሌቶች እንጂ ወንዶች ከማይሄዱበት ሲሄድ ሰውነቱ እየተሸማቀቀ ነበር። ጨለማን ተገን በማድረግ ነበር ብዙውን ሥራ የሚሠራው። በሣንቲም የገዛውን እነስተኛ ቀለብ ራሱ እየቀቀለ ለሦስትና ለአራት ቀን ነበር ቆጥቦ የሚበላው።